በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
በብሔራዊ አብዮታዊ ልማት ዘመቻና
የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ

የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ
ጽሕፈት ቤት

# በገጠር የጤና ጥናት 1974 – 1975
# የመጠይቅ አሞላል መመሪያ

ግንቦት 1974 ዓ.ም

316.3
ኢትዮ
MAN

ሰኔ 14 ቀን 1974 ዓ.ም.

## የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት

### ለጤና መጠይቅ አምሳል መመሪያ ማረሚያ

በጤና መጠይቅ መመሪያ ውስጥ ከነበሩት ስሕተቶች አብዛኞቹ በመመሪያው ውስጥ በስክሪኘቶ የታረሙ ቢሆንም ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁለት ማረሚያዎች ግን ረዘም ያሉ በመሆናቸው እንደ ሌሎቹ በመመሪያው ውስጥ ለማስተካከል ሊያስቸግሩ ስለሚችሉ ከዚህ በታች ተመልክቷል:-

1/ በገጽ 5፣ ለዓምድ 5 በተሠጠው መመሪያ መጨረሻ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ዓረፍተነገር ይቀጥላል:-
" ይህ ቀጥር ከቤተሰቡ የባለይዞታ መመዝገቢያ ቅጽ 75/0፣ ክፍል 2፣ ዓምድ 1 ውስጥ ካለው ተራ ቀጥር ለተመረጠው ቤተሰብ እንዳለ ተገልብጦ ይጻፋል"::

2/ በገጽ 5፣ ለዓምድ 6 በተሠጠው መመሪያ መጨረሻ ከዚህ በታች የተመለከተው ይቀጥላል:-

"ከምድብ አንድ /በግብርና ሥራ የተሠማራ አባል ካላቸው ቤተሰቦች/ ለተመረጡ ቤተሰቦች የሚሠጡት ተከታታይ ተራ ቀጥሮች ከባለይዞታ መመዝገቢያ ቅጽ 75/0፣ ክፍል 2፣ ዓምድ 9 ውስጥ በቀጥታ የሚገለበጡ ሲሆን፤ ከምድብ ሁለት /በግብርና ሥራ የተሠማራ አባል ከሌላቸው ቤተሰቦች/ ለተመረጡ ቤተሰቦች የሚሰጡት ተከታታይ ተራ ቀጥሮች ግን ከዚሁ ቅጽ፣ ክፍል 2፣ ዓምድ 10 ውስጥ በቀጥታ በመገልበጥ መጻፍ አለባቸው"::

# ማውጫ

…ት፡ መ/ጽ/ቤት፡
…ሕፍት፡
… Library


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ሀ — | መግቢያ | 1 |
| 1. | የጥናቱ ዓላማ | 1 |
| 2. | ጥናቱ የሚሸፍነው ሥፍራና የቤተሰብ ብዛት | 2 |
| 3. | ጥናቱ የሚካሄድበት ዙር ብዛት | 2 |
| 4. | ጥናቱ የሚወስከተው ጊዜ | 2 |
| 5. | የጥናቱ መጠይቅ የሚይዛቸው መረጃዎች | 2 |
| ለ — | የመጠይቁ አሞላል መመሪያ | 3 |
| 1. | ቆጣሪው ጥናቱ በሚካሄድበት ቤተሰብ የጥናቱን ተግባር ሲፈጽም የሚያሟላቸው ቅድመ ሁኔታዎች | 3 |
| 2. | በአጠቃላይ እያንዳንዱ ዓምድ ሲሞላ በጥንቃቄ መሞላት አለበት.. | 4 |
| ክፍል 1:— | የአካባቢ መለያ /ዓምድ 1—9/ | 4 |
| ዓምድ 1 | ክፍለ ሀገር | 5 |
| ዓምድ 2 | አውራጃ | 5 |
| ዓምድ 3 | ወረዳ | 5 |
| ዓምድ 4 | ገበሬ ማህበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ | 5 |
| ዓምድ 5 | የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር | 5 |
| ዓምድ 6 | የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር | 5 |
| ዓምድ 7 | የቤተሰቡ ምድብ | 5 |
| ዓምድ 8 | የጥናቱ ዙር | 6 |
| ዓምድ 9 | ወርና ዓመተ ምህረት | 6 |
| ክፍል 2:— | የቤተሰቡ የጤና ሁኔታ | 6 |
| ዓምድ 10 | ተራ ቁጥር | 6 |
| ዓምድ 11 | መደበኛ የቤተሰቡ አባላት ሙሉ ስም | 7 |
| ዓምድ 12 | ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና | 9 |
| ዓምድ 13 | ፆታ | 9 |
| ዓምድ 14 | ዕድሜ | 9 |
| ዓምድ 15—19 | ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች | 11 |
| ዓምድ 15 | በሽታ ደርሶብዎት ነበር /ባለፉት 14 ቀናት/ .... | 11 |
| ዓምድ 16 እና 17 | ለዓምድ 15 መልሱ "1" ከሆነ በሽታው ምን ነበር ወይም በሽታዎቹ ምን ምን ነበሩ? .... | 13 |

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | የጤና መታወክ ምልክቶች ስሜቶችና የበሽታዎች ስሞች ........ | 15 |
| ዓምድ 18 | በሽታው /ባለፉት 14 ቀናት/ ለስንት ቀናት ቆየባቸው? .... | 18 |
| ዓምድ 19 | በበሽታው ምክንያት /ባለፉት 14 ቀናት/ የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ .......................... | 19 |
| ዓምድ 20–23 | በአደጋዎች ምክንያት ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ ጉዳቶች | 20 |
| ዓምድ 20 | በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎታል /ማለት ባለፉት 14 ቀናት? .. | 20 |
| ዓምድ 21 | አደጋ ደርሶብዎት ከተጐዱ ለስንት ቀናት ቆዩብዎት? .......... | 21 |
| ዓምድ 22 | አደጋ ደርሶብዎት ከተጐዱ በጉዳቱ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ? .......................... | 21 |
| ዓምድ 23 | አደጋ ደርሶብዎት ከተጐዱ ጉዳቱን ያደረሰው ውጫዊ ምክንያት ... | 22 |
| ዓምድ 24 – 31 | ባለፉት 14 ቀናት በሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ከደረሰብዎት ለመፈወስ ከሚከተሉት የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? የሕክምና ዕርዳታ ካገኙ ያገኙበት ጊዜ ብዛት ............... | 23 |
| ዓምድ 24 | የሕክምና ዕርዳታ አገኙ /ባለፉት 14 ቀናት/? .......... | 24 |
| ዓምድ 25 | ከሆስፒታል፣ የጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ የሕክምና ዕርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/ .............. | 25 |
| ዓምድ 26 | ከቀበሌ ጤና ተጠሪ የሕክምና ዕርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት/ባለፉት 14 ቀናት/ .......................... | 25 |
| ዓምድ 27 | ከመድኃኒት ቤት /ከፋርማሲ/ የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት/ .................... | 25 |
| ዓምድ 28 | ከባሕላዊ ሐኪም የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/ ...................... | 25 |
| ዓምድ 29 | ሐኪም ካልሆኑ ሰዎች የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/ .................... | 26 |
| ዓምድ 30 | እራሳቸውን አከሙ? /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ እራሳቸውን ያከሙበት ጊዜ ብዛት/ .......................... | 26 |
| ዓምድ 31 | ከሌላ /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ከሌላ የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት/ .......................... | 26 |
| ዓምድ 32 | በዓምድ 25 እና 26 መሠረት የሕክምና እርዳታ ካላገኙ ምክንያት | 26 |
| ዓምድ 33 | አብዛኛውን ጊዜ የት ነው የሚፀዳዱት /ዕዳሪ የሚወጡት/ ..... | 27 |

# ማውጫ


ገጽ

ዓምድ 34 እና 35 ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ብቻ .... 28
ዓምድ 34 ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ወልደዋል ? ................ 28
ዓምድ 35 ለዓምድ 34 መልሱ "አዎን" ከሆነ ማን አዋለድዎት ? ..... 28
ዓምድ 36 ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውሀ አብዛኛውን ጊዜ የሚያገኘው ከየት ነው ? ................................ 29
ዓምድ 37 ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው ለጤንነት አመቺ በሆነ መንገድ በተጠበቀ ውሀ ነው ? ...................... 29
ዓምድ 38 ቤተሰቡ ቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ አለው ? ............... 31
ዓምድ 39 ቤተሰቡ የማጠቀምበት መፀዳጃ ጉድጓድ አለው ? .......... 31
ዓምድ 40 የቤተሰቡ አባላት ከሚያድሩበት ቤት የቤት እንሰሳት ያድራሉ ? 32

የመረጃ ሰብሳቢው የመስክ ተቆጣጣሪውና የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ኃላፊ ስምና ፊርማ ........................ 33
የሚታወሱ ክንውኖች የተፈጸሙባቸው ወርና ዓ.ም ........... 34
መጠይቅ ................................ መጨረሻ

## በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም

## የገጠር ጤና ጥናት

### ሀ. መግቢያ፣

ጤናን በሚመለከት ለጊዜው ያሉት መረጃዎች ውስን ከመሆናቸውም በላይ በሽታ ነክ የሆኑ መረጃዎች የሚገኙት በአገሪቱ ውስጥ ካሉት ጥቂት የጤና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የጤንነት ማጣት ወይም መጉደል ለሚደርስባቸው ግለሰቦች ከሚያደርጉዋቸው ዘገባዎች ነው። ነገር ግን ከጤና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚገኙት መረጃዎች ቁጥራቸው አነስ ካሉ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች እየሄዱ ሕክምናን ለማግኘት ስለሚሞክሩ የጥቂት ሰዎች የጤንነት ሁኔታን ብቻ ያመለክታሉ። ስለዚህ በአገሪቱ ውስጥ ስለሚኖረው ሕዝብ ይበልጥ ሰፋ ያላቸው ጤናን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት የተቀናጀው የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም አካል የሆነ የጤና ሰርቬይ ማካሄድ አስፈልጓል፡፡

### 1. የጥናቱ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና ዋና ዓላማዎች የሕዝቡን የጤንነት ሁኔታ ለማሻሻል በአገር አቀፍና በክፍላተ ሀገር ደረጃ ለሚታቀዱትና ለሚቀየሱት የጤና ፕሮጀክት እስትራቴጂዎች መሠረት የሚሆኑና፣ እንደዚሁም የሕዝቡን ጤንነት ለማሻሻል የሚደረጉትን ፕሮግራሞች ሂደት ለመከታተልና ለመገምገም የሚረዱ መረጃዎችን ለማስገኘት ናቸው፡፡ በተለይ የዚህ ጥናት ዓላማዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ በልዩ ልዩ አካባቢዎችና ቦታዎች የበሽታዎችና የአደጋዎችን ዓይነቶችና ስርጭቶች ለማሳየት የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣

ለ/ ሰዎች በታመሙ ጊዜ የሕክምና እርዳታን ለማግኘት የት እንደሚሄዱ ወይም ምን እንደሚያደርጉ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፣

ሐ/ ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በሚመለከት ሕዝቡ ያለውን አስተያየት ለመግለጽ ከመርዳቱም በላይ በአሁኑ ጊዜ ለሕዝቡ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ከሕዝቡ ፍላጐት ጋር ምን ያህል እንደሚመጣጠን ለማሳየት፣

መ/ ቤተሰቦች የተሻለ ጤንነትን ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ አንዳንድ አገልግሎቶች (Sanitary facilities) ያሉዋቸው መሆኑንና ግለሰቦችም ለጤንነት መሠረታዊ የሆኑ አንዳንድ ልምዶችን (Sanitary practices) መገበየታቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ለማግኘትና እነኚህን መረጃዎች በልዩ ልዩ አካባቢዎች ከሚገኙት የጤንነት ደረጃዎች ጋር ለማስተያየት ወይም ለማዛመድ፣

ሠ/ወላድ ሴቶች በሚወልዱበት ጊዜ በምን ዓይነት የማዋለጃ አገልግሎት እንደሚጠቀሙ ለማወቅ፣:

2. <u>ጥናቱ የሚሸፍነው ሥፍራና የቤተሰብ ብዛት፣</u> (Coverage) ጥናቱ በአሥራሁለት ክፍላተ ሃገራት በናሙና በተመረጡ 500 ገበሬ ማሕበሮችና ሠፈራ ጣቢያዎች ይካሄዳል:: ጥናቱም በነዚሁ ሥፍራዎች በናሙና የተመረጡ ቤተሰቦችን ይሸፍናል::

3. <u>ጥናቱ የሚካሄድበት ዙር ብዛት</u> (Frequency) :- ጥናቱ በሁለት ዙሮች የሚካሄድ ሆኖ መጀመሪያው ዙር በነሐሴ 1974 ዓ.ም ተካሂዷል ሁለተኛው ደግሞ ከ6 ወር በኋላ ይካሄዳል፣ ጥናቱም ከስድስት ወር በኋላ የሚደገመው በጤንነት በኩል ያለውን ወቅታዊ (Seasonal) ለውጦችን ለመረዳት ነው::

4. <u>ጥናቱ የሚመለከተው ጊዜ</u> (Reference Period):- በሽታንና ጉዳትን በሚመለከት ጥናቱ የሚመለከተው ጊዜ ጥናቱ ከሚካሄድበት ቀን ጀምሮ ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት የደረሰውን በሽታ ወይም ጉዳት ያጠቃልላል::

5. <u>የጥናቱ መጠይቅ የሚይዛቸው መረጃዎች</u>:-

/ሀ/. <u>ስለያንዳንዱ ቤተሰብ አባል</u>:- መደበኛ የቤተሰብ አባላት ስም፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር ያለው ዝምድና፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ስለደረሱ በሽታዎች፣ በሽታ ደርሶባቸው ነበር፣ የበሽታው ዝርዝር፣ በሽታው በዚህ ወቅት ለስንት ቀናት ቆየባቸው፣ በበሽታው ምክንያት በዚህ ወቅት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ፣ ባለፉት 14 ቀናት በአደጋ ምክንያት ስለደረሱ ጉዳቶች፣ በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ነበር? ጉዳቱ በዚህ ወቅት ለስንት ቀናት ቆየባቸው፣ በጉዳቱ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ፣ የጉዳቱ ውጫዊ ምክንያት፣ ባለፉት 14 ቀናት በሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ሲደርስባቸው ለመፈወስ ከሚከተሉት እርዳታ አገኙ? ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት?

ሀ/ የጤና ተቋም /ሆስፒታል፣ የጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ/
ለ/ የቀበሌ ጤና ተጠሪ፣
ሐ/ ከመድሐኒት ቤት /ከፋርማሲ/፣
መ/ ባሕሊዊ አካሚ፣
ሠ/ አካሚ ካልሆኑ ሰዎች፣
ረ/ አራሳቸውን አከሙ፣
ሰ/ ሌላ

በተለይ ከጤና ተቋም ወይም ከቀበሌ ጤና ተጠሪ እርዳታ ካላገኙ ያላገኙበት ምክንያቱ? ፣ አብዛኛውን ጊዜ የት ነው የሚፀዳዱት፣ ሲሆን በመጨረሻም እድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸውን ሴቶች ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ወልደው እንደሆነ በመጠየቅ ከዚያም ልጅ መውለዳቸው ከተረጋገጠ ማን እንዳዋለዳቸው መጠየቅን ያጠቃልላል።

/ለ/ ስለቤተሰብ በአጠቃላይ፡- ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውሃ አብዛኛውን ጊዜ የሚያገኘው ከየት ነው? ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው ለጤንነት አመች በሆነ መንገድ በተጠበቀ ውሃ ነው? ቤተሰቡ የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ አለው ቤተሰቡ የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ጉድጓድ አለው? የቤተሰቡ አባላት ከሚያድሩበት ቤት የቤት እንስሳት ያድራሉ? የሚሉት ናቸው።

ለ. የመጠይቁ አሞላል መመሪያ፣

1. ቆጣሪው ጥናቱ በሚካሄድበት ቤተሰብ የጥናቱን ተግባር ሲፈጽም የሚያሟላቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣

1.1/ ማንኛውም ቆጣሪ ጥናቱ እንዲካሄድበት ከተመረጠ ቤተሰብ ወይም ቤት ሁሉ ጥናቱን ለማካሄድ ሲደረስ ሰላምታ በመስጠት፣ ቀጥሎም ራሱን ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር በማስተዋወቅና የመጣበትን ዓላማ በማስረዳት መጀመር ያስፈልጋል። ይህም ዓላማ ቀደም ሲል በገጽ 1 የተገለጸው የጥናቱ ዋና ዓላማ ሲሆን ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ለማስቀመጥ ይቻላል፡-

መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብን ጤንነት ለማሻሻል ያለውን ከፍተኛ ፍላጎትና ዓላማ ደረጃ በደረጃ በሥራ ለመተርጎም እንዲችል በየአካባቢው ያሉትን የበሽታዎችና በሰዎች ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ዓይነት፣ እንደዚሁም በሽታና በአደጋ ምክንያት ጉዳት የሚደርስባቸውን ሰዎች ብዛት ማወቅ ያስፈልገዋል። በተጨማሪም በሽታዎችና አደጋዎች በሰዎች ላይ

የሚደርሱበት ምክንያቶች ምን እንደሆኑና በሽታ ወይም በአደጋ ምክን ያት ጉዳት ሲደርስባቸው ሕክምናን ለማግኘት የሚሞክሩትን የማይሞክ ሩትን ሰዎች ብዛት ማወቅ ያስፈልገናል ። በአንዳንድ ገበሬ ማሕበራት ውስጥ ከሚገኙት ቤተሰቦች በናሙና በተመረጡ ጥቂት ቤተሰቦች ውስጥ የጤና ጥናት በማካሄድ በአጠቃላይ በአካባቢው የነዚህን ሁኔታዎች ለማወቅ ይቻላል። ስለዚህ ይህ ቤተሰብ የጤና ጥናት እንዲካሄድ ባቸው ከተመረጡት ቤተሰቦች አንዱ በመሆኑ ጥናቱ ዛሬ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ስለሚካሄድ ሁላችሁም ያላንዳች ማመንታት ተባበሩን በማለት ቀላል በሆነ መንገድ ማስረዳት ያስፈልጋል።

1.2/ ይህ ጥናት በአንድ ቤተሰብ በሚካሄድበት ጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ መገኘት ያለበት ሲሆን በተቻለ መጠን የቀሩትም የቤተሰቡ አባላት መገኘት አለ ባቸው። ዋናው ተጠያቂ ወይም መልስ ሰጭ የቤተሰቡ ኃላፊና ሚስት/ባል ሲሆኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች አባላትም ሊጠየቁና መልስ ሊሰጡ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ በሽታ የደረሰበት አባል በሽታው እንዴት እንደሚያደርገው ከኃላፊው ይበልጥ ለማስረዳት ይችል ይሆናል።

1.3/ ጥናቱ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በሚካሄድበት ጊዜ የቤተሰቡ አባላት ያልሆኑ እንደጎረቤት፣ ወዳጅ፣ ዘመድ .... ወዘተ የመሳሰሉ ሰዎች መገኘት የጥናቱን ጥራት ስለሚቀንሰው የቤተሰቡአባል ያልሆነ ማንም ሰው መገኘት የለበትም።

2. <u>በአጠቃላይ አያንዳንዱ ዓምድ ሲሞላ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፤</u>

2.1/ መልሱ በቃላት ብቻ የሚጻፍ ከሆነ በዚያ ዓምድ ውስጥ ለኮድ ቢተው በታ ውስጥ መጻፍ የተከለከለ ነው።

2.2/ በአጠቃላይ የመረጃዎች አመዘጋገብ በጥራት መሆን አለበት።

2.3/ የሚፈለገው መልስ በኮድ የሚጻፍ ከሆነ ትክክለኛውን ኮድ በመምረጥ በተገቢው ቦታ መጻፍ ያስፈልጋል፤

<u>ክፍል 1፡ የአካባቢ መለያ፤</u>

<u>ዓምድ 1–9 የአካባቢ መለያ</u>፡–

ይህ ክፍል ጥናቱ የሚካሄድበትን የክፍለ ሀገር፣ የአውራጃ፣ የወረዳ፣ የገበሬ ማህበር ስም፣ የቤተሰብ መለያ ቁጥር፣ የቤተሰብ ተከታታይ

የቤተሰቡ ምድብ

ተራ ቁጥር፣/ የጥናቱ ዙርና መጠይቁ የተሞላበት ወርና ዓመተ ምሕረት የሚመዘገቡበት ነው::

ዓምድ 1:- ክፍለ ሀገር፣

ጥናቱ የሚካሄድበት ያክፍለ ሀገሩ ስም ይጻፋል::

ዓምድ 2.- አውራጃ፣

ጥናቱ የሚካሄድበት የአውራጃ ስም ይጻፋል::

ዓምድ 3:- ወረዳ፣

ጥናቱ የሚካሄድበት የወረዳ ስም ይጻፋል::

ዓምድ 4:- ገበሬ ማሕበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ፣

ጥናቱ የሚካሄድበት የገበሬ ማሕበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ ስም ይጻፋል::

ዓምድ5:- የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር፣

ጥናቱ በሚካሄድበት የገበሬ ማሕበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ ለጥናቱ የተመረጡትን ቤተሰቦች የተሰጣቸው የቤተሰብ መለያ ቁጥር በዚህ ዓምድ መስፈር አለበት::

ዓምድ 6:- የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር፣

ይህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጡትን ቤተሰቦች ተራ ቁጥር እንደ አመራረጣቸው ቅደም ተከተል የሚያሳይ ነው:: ስለሆነም በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ "01" የሚል ተራ ቁጥር ተሰጥቶት በሁለተኛ ለተመረጠው "02" በመመዝገብ የቤተሰቦች ተከታታይ ተራ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሰፍራል:: ምሳሌ: በግብርና ሥራ የተሠማራ አባል ያላቸው የተመረጡ ቤተሰቦች ተራ ቁጥር ከ"01 እስከ "25" ሲሆን ምድብ ሁለት ለሆኑት ቤተሰቦች ግን ከ01." እስከ"05" ሊሆን ይችላል ማለት ነው::

ዓምድ 7:- የቤተሰቡ ምድብ፣

ከቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ እንደታየው ለጥናቱ የተመረጡ ቤተሰቦች በሁለት ምድብ ይመደባሉ:: ምድብ አንድ በግብርና ሥራ የተሠማራ የቤተሰብ አባል ያሉዋቸውን ቤተሰቦች የሚይዝ ሲሆን ምድብ ሁለት ደግሞ በግብርና ሥራ የተሠማራ የቤተሰብ አባል የሌላቸውን ቤተሰቦች ያጠቃልላል::

ስለዚህ የሚጠናው ቤተሰብ አመራረጥ ቅደም ተከተል የሚያሳየው ቁጥር በመመዝገቢያ ቅጽ 75/0 /የቤተሰብና የባለ ይዞታ መመዝገቢያ ቅጽ/ ክፍል 2 ዓምድ 9 /በገብርና/ ውስጥ ከተጻፈ "ምድብ አንድ"፣ ዓምድ 10 /በሌላ/ ውስጥ ከተጻፈ ደግሞ "ምድብ ሁለት" ስለሆነ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ትክክለኛው ኮድ ተመርጦ በዓምዱ ላይ ይጻፋል፡፡

1 = ምድብ አንድ

2 = ምድብ ሁለት

በመመዝገቢያ ቅጽ 75/0፣ ክፍል 2 ዓምድ 9 /በገብርና/ ውስጥ ያመራረጥ ቅደም ተከተል ቁጥር የተሰጣቸው ቤተሰቦች በዚሁ ቅጽ ክፍል 2 በዓምድ 3 /ካርድ ኮለም 17/ ውስጥ "1" የሚለው ኮድ የገባላቸው ሲሆን በዓምድ 10 /በሌላ/ ውስጥ የአመራረጥ ቅደም ተከተል ቁጥር የተሰጣቸው ቤተሰቦች ግን በዓምድ 3 ውስጥ "2" የሚለው ኮድ የተጻፈላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 8:- የጥናት ዙር፣

በዓመት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉትን ለውጦች ለመገምገም ይረዳ ዘንድ በገጠር የጤና ጥናት በሁለት ዙሮች ይካሄዳል፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓምድ ጥናቱ የተከናወነው በየትኛው ዙር እንደሆነ የሚያመለክት ቁጥር ይሰፍራል፡፡ በዚሁም መሠረት ለመጀመሪያው ዙር መለያ ቁጥር "1" ሲሆን ለሁለተኛው ዙር ደግሞ "2" ይሆናል፡፡

ዓምድ 9:- ወርና ዓመተ ምህረት፣

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የተካሄደበት ትክክለኛ ወርና ዓመተ ምህረት ይገባል፡፡ ለምሳሌ ጥናቱ ነሐሴ 3 ቀን 1974 ዓ.ም ቢካሄድ በንዑስ ዓምድ 21 እና 22 ጥናቱ የተካሄደበትን ወር ማለት ነሐሴ መሆኑን ለማመልከት 12 ይመዘገባል ዓ.ም ለማመልከት ደግሞ በንዑስ ዓምድ 23 እና 24፣74 ይመዘገባል፡፡

ክፍል 2:- የቤተሰቡ የጤና ሁኔታ፣

ዓምድ 10:- ተራ ቁጥር ፣

ይህ ዓምድ ብዛታቸው 10 ወይም ከዚያ በታች የሆኑ የቤተሰብ አባሎችን ለመመዝገብ ተዘጋጅቷል፡፡

ነገር ግን የቤተሰቡ አባሎች ቁጥር ከ 10 በላይ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ፍርሞች እንደ አስፈላጊነቱ በመጠቀም በተጨማሪው ፍርም ከዓምድ 1–9 ያለውን ከመጀመሪያው ፍርም በመገልበጥ ይሞላል:: ከዚያም ዓምድ 10 ላይ ከዚህ በፊት የታተመውን ተራ ቁጥር 01፣ 02 ፣ 03፣ .... ወዘተ ሰርዞ 11፣ 12፣ 13፣ ... ወዘተ በማድረግ መለወጥ አለበት::

## ዓምድ 11 – መደበኛ የቤተሰቡ አባላት ሙሉ ስም፣

በቅድሚያ "ቤተሰብ" ማለት ምን ማለት መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል:: ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ ሁልጊዜ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማዕድ ቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡትን ሰዎች ያጠቃልላል፡ የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል:: በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች የባል ወይም የሚስት አባት፣ እናት፣ እህት ወንድም ሲሆኑ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱት የቤተሰብ አባሎችም ዘበኞች፣ የቤት ሠራተኞች፣ ጥገኞች ወዘተ ... ናቸው::

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል:: ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል፡ ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘበኞች፣ ጥገኞች ወዘተ .... ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ:: ነገር ግን ጥናቱ ከሚፈጸምበት ቀን በፊት ቤተሰቡን ትቶ ለእንግድነት ወደ ሌላ ቤተሰብ ሄዶ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ በኋላ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው:: ጋብቻው በአንድ ሚስት ላይ ብቻ የተመሠረተ ከሆነ አንድ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን /የቤት ሠራተኞች .../ ሊያጠቃልል ይችላል:: ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ /ማለት አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት/ የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ወዘተ... በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩ፣ ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፣ እያንዳንዳቸው የሰውየው ሚስቶች እንደ ልዩ ቤተሰብ መቆጠር አለባቸው:: በዚህ ሁኔታ ባልየው አሁን ካለችው ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር እንደ ቤተሰብ አባል ሲቆጠር፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ወዘተ .... ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ ስለአላቸው ከልጆቻቸውና

ከቀሩት ጥገኞቻቸው ጋር ለየራሳቸው እንደ ቤተሰብ ይቆጠራሉ፡፡

ስለዚህ፡ የቤተሰብን ትርጉም ለይታችሁ ካወቃችሁ በኋላ የያንዳንዱን የቤተሰብ መደበኛ አባል ሙሉ ስም በዚህ ዓምድ ይጻፋል፡፡ የቤተሰብ መደበኛ አባላት የሚባሉትም ከዚህ በታች ተመልክተዋል፡፡

ሀ. አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩና በቆጠራው ቀን እቤት የተገኙ ሰዎች ሁሉ እንደ አንድ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ፡፡

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ፣ በቆጠራው ቀን ለጥቂት ጊዜ/ ከስድስት ወር ያነሰ/ ከቤተሰቡ የተለዩ ሰዎች ለተለዩበት ቤተሰብ አባሎች ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ በዕረፍት ላይ ያሉትን፣ ለዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱትን፣ ዘመድ ለመጠየቅ የተጓዙትን፣ ለጥቂት ጊዜ ሆስፒታል የሚቆዩትን፣ በሥራ ምክንያት በጉዞ ላይ ያሉትንና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሐ. አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ የቤት ሠራተኞች፣ ዘበኞች፣ የቀን ሠራተኞች ..... ወዘተ ሌላ መኖሪያ ቤት ከሌላቸው ከሚሠሩበት ቤተሰብ ጋር አባሎች ይሆናሉ፡፡

መ. በአጠቃላይ አንድ ሰው ከአንድ ቤተሰብ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከስድስት ወር በላይ ከቆየ፣ ይህ ሰው በተጠቀሰው ቤተሰብ እንደ ቋሚ ወይም የሁል ጊዜ አባል ይቆጠራል፡፡

ሠ. አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከስድስት ወር በታች የተቀመጡ ከሆነ፣ እነኚህ ሰዎች ሌላ መኖሪያ ከሌላቸው በቆጠራው ቀን ከተገኙበት ቤተሰብ ጋር አባሎች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት ሴት ልጅ አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ተለይታ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ ስድስት ወር ባይሞላትም እንኳን ከባሏ ቤተሰብ ጋር መቆጠር አለባት፡፡

ስለዚህ በዓምድ ፲፩ የቤተሰቡ መደበኛ አባሎች የሆኑት ሙሉ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ ምዝገባ በሚከናወንበት ጊዜ በመጀመሪያ መስመር የቤተሰቡ ኃላፊ፣ በሁለተኛው ሚስት፣ /ባልየው/፣ በሶስተኛው ያላገቡ ልጆች / በዕድሜ ቅደም ተከተል/፣ ቀጥሎም ያገቡ ልጆች /ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩ ማለት ቋሚ አባሎች ከሆኑ፣/ ዘመዶቻቸው፣ ጥገኞቻቸው፣ ሠራተኞቻቸው፣ ወዘተ.... ይመዘገባሉ፡፡

ማሳሰቢያ፡ በቅርብ ጊዜ የተወለደ ሕፃን ለጅ ካለ ሳይረሳ መመዝገብ ይገባል፡፡ ሕፃኑ ገና ስም ያልወጣለት ከሆነ "ሕፃን" በማለት ይመዘገባል፡፡

ዓምድ 12:- ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና፣

የቤተሰቡ ኃላፊ ማለት በሌሎች የቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚታየው ሰው ነው፡፡ የአንድ ቤተሰብ ኃላፊ በጾታ ስለማይወሰን የቤተሰቡ ኃላፊ ወንዷ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ኃላፊው በቤተሰቡ ውስጥ ከሚገኙት አባሎች በዕድሜ ላይበልጥ ይችላል፡

በዓምድ 11 የቤተሰቡ አባሎች በሙሉ ከተመዘገቡ በኋላ እያንዳንዱ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለውን ዝምድና መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በዓምድ 12 ለቤተሰቡ ኃላፊ "ኃላፊ" የሚል ቃል ብቻ ይጻፍለታል፡፡ ለቀሩት ግን ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ትክክለኛ ዝምድና ይገለጻል፡፡ ለምሳሌ ሚስት/ባል፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ እናት፣ ወንድ አያት፣ ሴት አያት፣ ወንድም፣ እህት፣ የሚስት እህት፣ የወንድም ሚስት፣ የወንድም ልጅ፣ አክስት፣ አጐት የቤት ሠራተኛ፣ ዘበኛ፣ ወዘተ .... የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ዓምድ 13:- ጾታ፣

ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚከተሉትን ኮዶች በመከተል ጾታው በዚህ ዓምድ በትክክል ይሠፍራል፡፡

1 = ወንድ
2 = ሴት

የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ጾታ በዓምድ 11 ከተጻፈው ስምና በዓምድ 12 ውስጥ ከተገለጸው ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና ጋር መስማማቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የሕፃናትም ጾታ ሲመዘገብ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ዓምድ 14:- ዕድሜ፣

ጥናቱ እስከ ተደረገበት ዕለት ድረስ የያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ዕድሜውን በጥንቃቄ በመጠየቅ በሙሉ ዓመት በዓምዱ ይመዘገባል፡፡ ለምሳሌ የገለ አንድ ሰው ዕድሜው 13 ዓመት 11 ወር ከ3 ሳምንት ከሆነ፣ የሰውየው ዕድሜ በዓመት ስሩ ዕድሜ 13 ዓመት ብቻ መሆኑ ይገለጽ፡፡ የሰውየው ዕድሜ በዓመት በወርና በሳምንት የተሰጠ ከሆነ ዕድሜው በሙሉ ዓመት ብቻ ይመዘገባል፡፡

ወደሚቀጥለው ዓመት ማጣጋት አያስፈልግም:: አንድ ሕፃን ልጅ ዕድሜው ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ "00"፣ አንድ ዓመት ሞልቶት ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ ደግሞ "01" በማለት ይጻፋል:: የአንድ ልጅ ዕድሜ 2 ዓመት አልፎት ከ3 ዓመት በታች ከሆነ "02" በማለት ዕድሜው ይገለጻ፣ የቤተሰቡ አባል ዕድሜው 98 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ "98" ይመዘገብለታል::

የያንዳንዱን አባል ዕድሜ ለማግኘት በተቻለ መጠን መሞከር ያስፈልጋል:: ዕድሜያቸውን ለማስታወስና ለመገመት እንዲችሉ በተለያዩ ዘዴ መርዳትና ማበረታታት አስፈላጊ ይሆናል:: አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን ለመናገር የማይፈልጉ አሉ:: እንዲያውም ስማቸው እንደተመዘገበ ካወቁ ዕድሜያቸውን ለመናገር አይፈቅዱም:: ቢሆንም ከዚህ በታች የአንዱን ሰው ዕድሜ ለመገመት እንዲሁም የጠያቂዎችን ተባባሪነት ለማግኘት የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች ተጠቅሰዋል::

ከቤተሰቡ አባሎች መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይሆናል:: ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ ትልቅ ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ካለ፣ የእናት ዕድሜ ቢያንስ 28 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል:: የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነጻጸር ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል:: ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት ወይም ሶስት ዓመት ይወልዳሉ:: የትንሹ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የታላቁ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል:: ዕድሜአቸው የገፋ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል:: የነኚህ ሰዎች ዕድሜ ከትልቅ ልጆቻቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል:: ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነውን ግምት መጻፍ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም አንድ አባል ባገቡበት ጊዜ ዕድሜያቸው ስንት እንደነበረ፣ ተጋብተው ስንት ዓመት እንደቆዩና እንደዚሁም ከልጆቻቸው ዕድሜ ጋር በማዛመድ ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል:: በተጨማሪም የአንድ ቤተሰብ አባል የተወለደበትን ዓመት ከአንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር በማዛመድ ዕድሜውን ለመገመት ስለሚቻል አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ዓመት ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ቀርቧል::

አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል:: እርግጥ አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ ወዘተ... ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለጽ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛ ዕድሜያቸው መሆኑን በመገንዘብ ይህንኑ ለማግኘት መሞከር በጣም አስፈላጊ ነው::

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት ቁጥር በዚህ ዓምድ መጻፍ አለበት::

## ዓምድ 15 – 19:- ባለፈት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች፤

በሽታ ማለት የአካል ወይም የአእምሮ ደህንነት ሚዛን መጓደል ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር በሽታ የጤንነት መጓደል ወይም አለመሟላት ማለት ነው:: ማንኛውም ሰው ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ ለአጭር ጊዜ /ለአንድ ሰዓት/ እንኳ ቢሆን በሽታ ይዞት እንደነበረ ከገለጸ በሽታ ይዞት እንደ ነበረ ይቆጠራል:: ስለዚህ ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ጥናቱ ከሚካሄድበት ዕለት ጀምሮ ወደ ኋላ በመቁጠር ባለፈት 14 ቀናት በሽታ የደረሰበት መሆኑ ወይም አለመሆኑ፤ ታሞ ከነበረስ የበሽታው ዓይነት፤ በሽታው ለስንት ቀን እንደቆየበት እና በበሽታው ምክንያት የዘወትር ተግባሩን አቋርጦ የሰነበተበት ቀናት ብዛት በእነዚህ 5 ዓምዶች ውስጥ ይመለከታሉ:: አንድ ሰው ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ በአንድ ጊዜ ወይም በተለያዩ ጊዜያት ከአንድ በበለጡ በሽታዎች ሊጠቃ ስለሚችል ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እስከ ሁለት በሽታዎች ለመመዝገቢያ ቦታዎች ተሰጥቷል::

ያለፈት 14 ቀናት ሲባል ምን ያህል ወደ ኋላ መቁጠር እንዳለባቸው ወይም ከመቼ ጀምሮ መሆን እንዳለበት ለብዙ መልስ ሰጪዎች በትክክል ግልጽ ላይሆን ይችላል:: ስለዚህ በማያጠራጥር ሁኔታ ግልጽ እንዲሆንላቸው ጥያቄዎች በጥንቃቄና ቀላል በሆነ መንገድ መቅረብ አለባቸው:: ለምሳሌ ቤተሰቡ የሚጠናው ሰኞ ከሆነ ከዚህ ዕለት ጀምሮ ባለፈት 14 ቀናት በሽታ ደርሶብዎት ወይም ታመው ነበር ወይ? የጥናቱ ቀን ሐሙስ ከሆነም ከዚህ ዕለት በፊት በነበሩት 14 ቀናት ውስጥ በሽታ ደርሶብዎት ነበር ወይ? ወይም ባለፈት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ታመው ነበርን? ወይም ቤተሰቡ የሚጠናው በነሐሴ 5 ቀን 74 ዓ.ም ከሆነ ከሐምሌ 20 ቀን 1974 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በሽታ ደርሶብዎት ነበርን? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል:: ጥናቱ የሚካሄደው በሌላ ቀንም ቢሆን እንደዚሁ:: ከዚህ የበለጠ ማብራራት የሚያስፈልግበት ጊዜም ሊኖር ይችላል::

## ዓምድ 15:- በሽታ ደርሶብዎት ነበር?/ባለፈት 14 ቀናት/

ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ አንድ ሰው ታሞ ነበር የሚባለው በሽታው በዚህ ወቅት የጀመረው የሆነ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን በሽታው ቀደም ብሎ የያዘው ቢሆንም

ባለፉት 14 ቀናትም ውስጥ ከቀጠለ. ያው በዚህ ወቅት ታሞ እንደነበረ መቁጠር አለበት:: ዋናው ነገር በሽታው መቸም ይጀምር ባለፉት 14 ቀናት ለተወሰኑ ሰዓቶች ወይም ቀናት ሰውየው በሕመም ላይ መኖሩ ነው:: በሽታ ሲባል ማንኛውም በሽታ መሆኑን አለመዘንጋት ነው:: በሽታው ረጅም ጊዜ የቆየ (Chronic) ወይም ለአጭር ጊዜ አጥቅቶ የሚለቅ ዓይነት ሊሆን ይችላል::

ማንኛውም የቤተሰብ አባል ጥናቱ ከሚደረግበት ዕለት በፊት በነበሩት 14 ቀናት ውስጥ መታመሙን ከገለጸ መልሱ "አዎን" ይሆናል:: ነገር ግን ባለፉት 14 ቀናት በሽታ ካልደረሰበት ትክክለኛ መልሱ "የለም" ነው:: ስለ ዚህ "አዎን" ወይም "የለም" በማለት ፈንታ ከሚከተሉት ኮዶች ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ 15 መጻፍ አለበት፦

አዎን = 1　　　የለም = 2

በሽታዎች ያሉባቸው አንዳንድ ሰዎች /በተለይ በሽታዎቹ የቆዩ ከሆኑ/ በሽታ ያለባቸው መሆኑን ሊዘነጉ ስለሚችሉ የቆየ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት የጀመረ ነገር ግን ያልዳነ፣ .... ወዘተ. በሽታ ባለፉት 14 ቀናት አልነበረብዎትም ወይ? እያሉ ሳያጠሩ "የለም" የሚለውን መልስ መቀበል አያስፈልግም:: በመልስ ሰጭዎች ሊረሱ የሚችሉ በሽታዎች ለምሳሌ ያህል አዝማ፣ የቆየ የአባለዘር በሽታ፣ እንቅርት፣ የሚጥል በሽታ፣ የቆየ ቁርጥማት፣ የአእምሮ በሽታ /እብደት/፣ የልብ ድካም፣ የሥጋ ደዌ በሽታ፣ የጉበት በሽታ፣ የኩላሊት በሽታ፣ የተጓደለ አመጋገብ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የስኳር በሽታ፣ .... ወዘተ. የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ አንዱ ሰው በዚህ ወቅት በሽታ አልደረሰብኝም ሲል ወይ የልብ ድካም ወይ የቆየ ቁርጥማት፣ .... ወዘተ. የለብዎትም፣ አልነበርዎትም፣ የለበትም፣ የለባትም እያሉ በተጨማሪ መጠየቅ ያስፈልግ ይሆናል::

ነገር ግን በአደጋ ምክንያት የደረሰ ጉዳት እንደ በሽታ እንዳይ ቆጠር መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ አንድ ሰው ወድቆ እጁን ቢለ ተሰበረ በመታከም ላይ ቢሆን ጉዳት ነው እንጂ በሽታ ስላልያዘው እንደታመመ አይቆጠርም:: ስለዚህ ወድቆ እጁን ከመሰበሩ በቀር በተጨማሪ በሽታ ያልደረሰበት ከሆነ ምንም በሽታ እንዳልደረሰበት መቁጠር አለበት:: ለዚህ ሁኔታ መልሱ የለም ስለሆነ "2" መጻፍ አለበት:: እንደዚሁም በሬ ወግቶት፣ አውሬ ነክሶት፣ መርዝ ወስዶ፣ ጎርፍ አንገላቶት፣ .... ወዘተ. አንድ ሰው ጉዳት ቢደርሰበት በሽታ እንደያዘው መቆጠር የለበትም::

## ዓምድ 16 እና 17:- ለዓምድ 15 መልሱ "1" ከሆነ በሽታው ምን ነበር ወይም በሽታዎቹ ምን ምን ነበሩ?

ባለፉት 14 ቀኖች ውስጥ በሽታ ይዞት እንደነበር ለገለጸ ወይም ለታወቀ ማንኛውም የቤተሰብ አባል /ማለት በዓምድ 15 የሠፈረው መልስ "1" ከሆነ/ የበሽታው/የበሽታዎቹ/ ዓይነት /ስም/ በነዚህ ዓምዶች መጻፍ አለበት:: ይኸውም በሽታው አንድ ብቻ ከሆነ ሁለቱን ዓምዶች መጠቀም ስለማያስፈልግ የመጀመሪያው /ዓምድ 16/ ብቻ ይበቃል:: ሁለቱን ዓምዶች /ዓምድ 16 እና 17/ መጠቀም የሚገባው ለአንድ ሰው ሁለት በሽታዎችን መመዝገብ ሲያስፈልግ ብቻ ነው:: አንድ ሰው በተባለው ወቅት ከሁለት በበለጡ በሽታዎችም ሊጠቃ ይችላል:: ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለታማሚው ይበልጥ ሐይለኛ ስለሆኑት ሁለት በሽታዎች ብቻ መሆን አለበት::

የበሽታዎችን ዓይነት በትክክል ለመለየት ይረዳ ዘንድ ተለይተው ሊታወቁ የሚፈለጉ በሽታዎች ስም ዝርዝር ከነመለያ ምልክቶቻቸው (symptoms) ከዚህ በታች ይገኛል:: በዝርዝሩ ውስጥ በሽታዎቹ በ8 ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለዋል:: በያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ደግሞ ጥቂት በሽታዎች ከነመለያ ምልክቶቻቸው (symptoms) ተዘርዝረዋል::

ስለዚህ እያንዳንዱ በሽታ የያዘውን ሰው በሽታው አንድ ብቻ ከሆነ እንዴት እንደሚያደርገውና እንደሚሰማው ወይም ሲያደርገውና ሲሰማው እንደነበረ በመጠየቅ በዚህ የበሽታዎች ዝርዝር ከተሠጡት ምልክቶችና ስሜቶች ጋር በማገናዘብ መጀመሪያ ከስምንቱ ዋና ዋና ክፍሎች በሽታው ከየትኛው ክፍል መመደብ እንዳለበት፣ በክፍሉ ውስጥ ደግሞ የትኛው በሽታ እንደሆነ በማጣራት የበሽታውን ስም በዓምድ 16 ውስጥ በተሠጠው ቦታ ላይ መጻፍ ነው:: ባለፉት 14 ቀናት ሁለተኛ በሽታ እንደነበረበት ከተረጋገጠ ደግሞ ከፍ ብሎ በተገለጸው መንገድ በሽታው ምን እንደሆነ በማጣራት የበሽታውን ስም በዓምድ 17 ውስጥ መጻፍ ነው::

ታማሚው ሰው ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ እንደዚህ ሲያደርገኝ እንዲህ ሲሰማኝ ነበር ብሎ የሚገልጻቸው ምልክቶች የሚገናዘቡት በዝርዝር ውስጥ ከተሠጡት በሽታዎች መካከል ከአንድ ብቻ ሳይሆን

የሁለት ወይም የሶስት በሽታዎችን ምልክቶች የሚያጣምሩ ከሆነ በዝርዝሩ በተሰጡት ምልክቶች በመመራት አንዱንበሽታ ከሌላው መለየት ያስፈልጋል:: ይህም ሲሆን ለታማሚው ሰው ይበልጥ ኀይለኛ በሆኑበት ሁለት በሽታዎች ላይ ብቻ ማተኮር ያስፈልጋል:: ከሁለቱም ይበልጥ ከባድ የሆነው በሽታ ስም በዓምድ 16 ሲመዘገብ የሁለተኛው በሽታ ስም ደግሞ በዓምድ 17 ይጻፋል::

አንዳንዱ ሰዎች የያዛቸውን በሽታ ስም ይናገሩ ይሆናል:: እርግጥም አንዳንድ በሽታዎች በአገሬው ተለይተው ሊታወቁ ይችሉ ይሆናል:: ለምሳሌ የወባ በሽታን ብዙዎች በትክክል እንደሚለዩት ይገመታል:: ሆኖም መልስ ሰጪዎች አንድን አባል ያጠቃ የበሽታ ስም ሲሰጡ እንዳለ ተቀብሎ መመዝገብ ፈጽሞ አይገባም:: መጀመሪያ የተባለው በሽታ በዝርዝሩ ውስጥ መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ በተጨማሪ በሽታው ታማሚውን እንዴት እንደሚያደርገውና ምን ስሜቶች እንደሚሰሙት ጠይቆ በዝርዝሩ ውስጥ ለበሽታው ከተዘረዘሩት ምልክቶችና ስሜቶች ጋር መስማማታቸውን ካረጋገጡ በኋላ መመዝገብ ይገባል:: ታማሚው የሰጠው ምልክቶችና ስሜቶች የጠቀሰው በሽታ ከሚያስከትላቸው ምልክቶችና ስሜቶች ጋር ካልተስማሙ ግን በዝርዝሩ ምልክቶችና ስሜቶች ተመሳሳይ የሆነ የሌላ በሽታ ስም መመዝገብ ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪው ምች መታኝ፣ መጋኛ መታኝ .... ወዘተ ቢል እንዴት ያደርግሃል.. እያሉ በመጠየቅ የበሽታውን ምልክቶች አውቆ ዝርዝሩ ውስጥ ከተሠጡት ጋር በማገናዘብ መለየት ነው እንጂ እንዲሁ መተው ወይም ምች .... ብሎ መጻፍ አይገባም::

## የጤና መታወክ ምልክቶች፣ ስሜቶችና የበሽታዎች ስሞች

### 1. ትኩሳት

1.1 ከፍተኛ እያቋረጡ የሚመለስ ትኩሳት ከማንቀጥቀጥ፣ ብርድ ብርድ ማለት ጋርና የሰውነት ድካም፣ ______________________ "ወባ"

1.2 ትኩሳትና ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሰውነት የሚጠፋ ሽፍታ ጋር፣ ______ "ኩፍኝ"

1.3 ትኩሳት ከማቅለሽለሽና ዓይን ብጫ መሆን ጋር ቀለሙ የነጣ ሰገራ፣ መገጣጠሚያ ላይ ቁርጥማት ትውከት፣ ምግብ ማስጠላት፣ ______________ "የወፍ በሽታ"

1.4 ትኩሳት ከአንገት/ መገተር ጋር፣ ትውከት እንዲሁም በሰውነት ላይ የሽፍታ ምልክት፣ ______________________ "አንገት ገትር"

1.5 ትኩሳት ከከባድ ራስ ምታት ጋር አንዳንድ ጊዜ ሰውነት መሳት፣ ድካም፣/ ብዙውን ጊዜ በወረርሽኝ መልክ የሚዛመት/፣ ______________ "ተስቦ"

1.6 ሌላ ከላይ ያልተገለጹ የትኩሳት በሽታዎች፣ ለምሳሌ ጉድፍ ....ወዘተ "ሌላ ትኩሳት"

### 2. ሳል

2.1 ለረጅም ጊዜ /3 ወር ወይም በላይ/ የቆየ ሳል ከወፍራም አክታ /ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል/ ከሰውነት ክብደት መቀነስ ጋር አንዳንድ ጊዜ መጠነኛ ትኩሳትና ሌሊት ማላብ፣ ______________ "ሳምባ ነቀርሳ"

2.2 ለአጭር ጊዜ የቆየ /ከ3ወር ያነሰ/ ሳል፣ ትኩሳትና በደረት ዙሪያ ውጋትና ትንፋሽ ማጠር ጋር አክታ፣ ______________ "ሎንያ"

2.3 ኃይለኛ /አጣዳፊ/ ሳል ከትኩሳትና ትክትክ ጋር ብዙውን ጊዜ ከ5 ዓመት በታች በሆኑ ልጆች የሚታይ፣ ______________ "ትክትክ"

2.4 ሌላ ከላይ ያልተገለጹ የሳል በሽታዎችና ስሜቶች ለምሳሌ ጉንፋን፣ ትንፋሽ ማጠር፣ አዝማ፣ ውጋት ..... ወዘተ __________ "ሌላ ሳል"

## 3. ተቅማጥና የሆድ በሽታ

3.1 የሚያጣድፍ ቀጭን ዓይነ ምድር፣ ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል አንዳንድ ጊዜም ንፍጥ የሚመስል አጓሬ ...ወዘተ ______________________ "ተቅማጥ"

3.2 በቀን ከ3 ጊዜ የበለጠ ተቅማጥ ከትውከት/ ጋር ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት።
______________ "ጋስትሮ_ኢንትራይቲስ"

3.3 እንደ ወስፋት፣ ኮሶ የመሳሰሉት በበሽታኛው የታዩ የሆድ ትላትሎች።
______________ "የጥገኛ_የሆድ_ትላትል"

3.4 ሌላ ተቅማጥና የሆድ በሽታ ምሳሌ የጨጓራ በሽታ፣ ሆድ መንፋት ......፡ ወዘተ ______________________ "ሌላ_ተቅማጥና_የሆድ_በሽታ"

## 4. አንገትና እራስ ላይ የሚታዩ በሽታዎች

4.1 በአንገት ላይ ከፊት በኩል በውጭ የሚታይ ስቃይ የሌለበት/ የማያም/ እብጠት በተለይም ምራቅ፣ ውኃ፣ ምግብ ሲወጡ ወደ ላይና ታች የሚንቃነቅ፣ ______________________________ "እንቅርት"

4.2 አንዳንድ ጊዜ መግል ያለው የጆሮ መታመም /የቆየ ያለመስማት፣ ችግርን አይጨምርም።/ ______________________ "የጆሮ_ሕመም"

4.3 የዓይን መታመም ከዓይን አር ጋር ሊሆን ይችላል። /የአንድ ወይም የሁለት ዓይኖች መታወርን አይጨምርም።______________________ "የዓይን_ሕመም"

4.4 በህጻናት ላይ የሚገኝ የጉሮሮ ህመም አንዳንድ ጊዜ በአንገት አካባቢ ከፊት በኩል ከውጭ /ከፍ ብሎ/ የሚታይ ሕመም ያለበት እብጠት፣ የመዋጥ ችግር ትውከት፣ ትኩሳት፣ ____ "የጉሮሮ_ሕመም"

4.5 የጥርስና የድድ ህመም። ______________________ "የጥርስና_የድድ_ሕመም"

4.6 ሌላ የአንገትና የራስ በሽታ ምሳሌ ራስ ምታት፣ ነስር፣ ጆሮ ደግፍ ....... ወዘተ. ______________________ "ሌላ_የአንገትና_የራስ_በሽታ"

5. የአባለዘር በሽታ

5.1 በሴቶች ወይም በወንዶች ላይ የሚታይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚመጡ በሽታዎች ምሳሌ ጨብጥ፣ ቂጢኝ፣ በብልት ላይ ወይም አካባቢ ቁስል፣ አብጠት ..... ... ወዘተ ____ "የአባለ ዘር በሽታ"

6. በቆዳ ላይ የሚታይ በሽታ

6.1 አደጋ ሳይደርስ በቆዳ ላይ የሚታዩ ቁስሎች እከክ፣ ችፌ፣ ቁስል ...... ....... ወዘተ. ____ "በቆዳ ላይ ቁስል"

6.2 "የስጋ ደዌ" ____ "የስጋ ደዌ"

6.3 በአንድ እግር ወይም በሁለቱ እግሮች ወይም በብልት ፍሬዎች ላይ የቆየ በጣም ትልቅ ዕብጠት ____ "ዝሆኔ"

6.4. ሌላ በቆዳ ላይ፣ የሚታዩ በሽታዎችና ስሜቶች ለምሳሌ ለምጥ፣ አባ ሰንጋ፣ ......... ወዘተ ____ "ሌላ የቆዳ ላይ በሽታ"

7. በተለይ ነፍሰ ጡሮችን፣ አራሶችንና ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ሴቶችን ሁሉ የሚመለከቱ የጤና ችግሮች፣

7.1 የጤና መታወክ ያለበት እርግዝና/ለምሳሌ ከማህፀን ወይም ከብልት ደም መውጣት፣ እግር ማበጥ፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ መገርጣት፣ ... ወዘተ ____ "ውስብስብ እርግዝና"

7.2 ከሰባት ወር ዕርግዝና በፊት የሆነ ውርጃ፣ ____ "ውርጃ"

7.3 በወሊድ ጊዜ የጤና ችግር ለምሳሌ በወሊድ ጊዜ ከመጠን በላይ ደም መፍሰስ፣ ረጅም ጊዜ የወሰደ አድካሚ ምጥ፣ ____ "አስቸጋሪ ወሊድ"

7.4 ከወሊድ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ በወሊድ ምክንያት የጤና ችግር ለምሳሌ ትኩሳት ____ "የአራስ የጤና ችግር"

7.5 "የወር አበባ በሽታና ሌሎች የእናቶች በሽታዎች፣" ____________________ "የወር አበባ በሽታና ሌሎች የእናቶች በሽታዎች"

## 8. ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ በሽታዎች

8.1 የሰውነት መክሳት ከሀይል ማጣት ጋር የሰውነት ማበጥ፣ በደም ማነስ መገርጣት፣ የራስ ጠጕር ቀለም መለወጥ በተለይ የሕፃናት በሽታ፣ ________ "የተጓደለ አመጋገብ"

8.2 የመንጋጋ አለከፈት ማለት ከጡንቻዎች መገታተር ጋር ቁስል የነበረው ወይም ያለው ወይም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተወለደ/ከወር ወዲህ/ወይም በቅርብ ጊዜ የወለደች/ከወር ወዲህ/ ____________________ "መንጋጋ ቆልፍ"

8.3 የአእምሮ በሽታ ለምሳሌ እብደት፣ ____________________ "እብደት"

8.4 ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የጤና በሽታዎች ለምሳሌ አጠቃላይ ድካም፣ ልብ ድካም፣ ቁርጥማት፣ የኩላሊት በሽታ፣ የደም ብዛት፣ የደም ማነስ፣ የስኳር በሽታ ........ ወዘተ ______________ "ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ በሽታዎች"

## ዓምድ 18:- በሽታው /ባለፉት 14 ቀናት/ ለስንት ቀናት ቆየብዎት?

እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው ታማሚው ሰው በዓምድ 16 ውስጥ በተመዘገበው የበሽታ ዓይነት ወይም በዓምድ 16 እና 17 በተመዘገቡት በሽታዎችና ባልተመዘገቡም በሽታዎች ጥምር ሲሆን በጠቅላላው በበሽታ ምክንያት ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለስንት ቀናት እንደተጠቃ ነው። ይኸውም የሚሠፍረው የቀኖች ብዛት መሆኑ ነው። አንድ ሰው ሲታመም የግዴታ መተኛት ወይም ቤት ውስጥ መዋል አለበት ማለት ያለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በተለይ አንዳንድ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ወይም የሚቆዩ (Chronic ) በሽታዎች ያሉባቸው ሰዎች ከሞላ ጎደል በደንብ ለረጂም ጊዜ በሥራ ላይ ተሰማርተው ሊቆዩ ይችላሉ። በሽታው /በተለይ ክሮኒክ ከሆነ/ ካለፉት 14 ቀናት መጀመሪያ በፊት ብዙ ቀደም ብሎ የጀመረ ወይም የተነሳ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እዚህ የሚፈለገው ካለፉት 14 ቀኖች ታማሚው ለስንት ቀናት በበሽታ እንደተጠቃ ስለሆነ የሚመዘገበው የቀኖች ብዛት በምንም ዓይነት ከ14 ይበልጥ ሊሆን አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ባለፉት 14 ቀኖች ውስጥ ለአንድ

ቀን ወይም ከቀኑ ለጥቂት ሰዓቶች /ለአንድ ሰዓት እንኳ ቢሆን/ የታመመ ቢሆን ለአ
ንዱ ቀን እንደ ታመመ ተቆጥሮ በዓምድ 18 በሽታው ለአንዱ ቀን እንደቆየበት በማሰብ
"01" የሚል አኃዝ ማስፈር አስፈላጊ ነው፡ እንደዚሁም ሌላ ግለሰብ ለሦስት ሙሉ
ቀናትና በተጨማሪም በአራተኛው ቀን ለአንድ ሰዓት የታመመ ቢሆን ግለሰቡ ለአራት ቀን
የታመመ መሆኑን ለመግለጽ በዓምዱ ውስጥ መመዝገብ ያለበት "04" መሆን አለበት፡፡
ሌላ ሰው ደግሞ ባለፈት 14 ቀናት መጀመሪያ በአንድ በሽታ ምክንያት ለ5 ቀናት
ታሞ ከዳነ በኋላ እንደገና ሌላ በሽታ ይዞት ለ 7 ቀናት ቢቆይበት በጠቅላላው ለ12
ቀናት ስለ ታመመ የሚጻፈው "12" ነው፡፡ ከምሳሌዎቹ እንደሚታየው የቀኖቹ ብዛት
ከ10 በታች ከሆነ በስተግራ በኩል "0" በመጨመር ባለሁለት ዲጂት /አኃዝ/ አድ
ርጎ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 19፡- በበሽታው ምክንያት/ባለፈት 14 ቀናት/ የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ፡-

አንድ ሰው በማንኛውም ቀን የዘወትር ተግባር አለው፡፡ የዘወትር ተግባር የሚባለው አንድ ሰው በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት ባይተጓጎል ኖሮ በዚያን ቀን ወይም በነዚያ ቀኖች በአብዛኛው የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡ ለምሳሌ ሥራ መሥራት /እርሻ፣ ንግድ፣ ልብስ ስፌት፣ ማስተማር፣ ማከም... ወዘተ./ ትምህርት ቤት ሄዶ መማር፣ መጫወት/ በተለይ ለሕፃናት/ ሸማግሌ ከሆኑ ቤተክርስቲያን ወይም መስጊድ ሄዶ መጸለይ ..... ወዘተ. አንድን ሰው በሽታ ይዞት ከበረታበት የዘወትር ተግባሩን ከመፈጸም ሊያግደው ይችላል፡፡

የዘወትር ተግባሩን ከማከናወን የሚታገደው በበሽታው ምክንያት በመተኛት ወይም ቤት ውስጥ በመዋሉ ወይም ዓቅምና ብርታት ስላነሰው ወይም ሕክምና በመውሰድ ላይ በመሆኑ ነው፡፡

እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው አያንዳንዱ የታመመ ሰው በበሽታ ምክንያት ባለፈት 14 ቀናት የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ያልቻለባቸውን ቀናት ብዛት ነው፡፡ እዚህም ሊሠፍር የሚችለው የቀናት ብዛት በምንም ዓይነት ከ 14 መብለጥ የለበትም፡ በዓምድ 18 ውስጥ እንደተመለከተው የቀናቱ ብዛት ከ10 ያነሰ ከሆነ በስተግራ በኩል "0" በመጨመር ባለ ሁለት ዲጂት /አኃዝ/ አድርጎ መጻፍ ነው፡፡

## ዓምድ 20 -23:- በአደጋዎች ምክንያት ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ ጉዳቶች፣

ጥናቱ ከሚካሄድበት ዕለት ጀምሮ ወደ ኋላ በመቁጠር ባለፉት 14 ቀናት ማንኛውም የቤተሰብ አባል በሆነ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣ በአደጋ ምክንያት የደረሰው ጉዳት በሰውየው ላይ የሰነበተበት ቀናት ብዛት፣ በአደጋ ምክንያት በደረሰው ጉዳት ምክንያት የዘወትር ተግባሩን አቋርጦ የሰነበተበት ቀናት ብዛትና የጉዳቱ ዐቢይ ምክንያት ምን እንደሆነ በእነዚህ አራት ዓምዶች ውስጥ ይመለከታሉ:: አሁንም በዓምድ 15 እስከ 19 እንደተደረገው ሁሉ ያለፉት 14 ቀናት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለመልስ ሰጪዎች በደንብ ግልጽ እንዲሆንላቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: ሕፃናትን በሚመለከት መልሱን ከእናት አባት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካለው አባል ማግኘት ይገባል::

## ዓምድ 20:- በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎታል /ማለት ባለፉት 14 ቀናት/?

እዚህ ላይ በሽታዎች በአደጋዎች ምክንያት እንደደረሱ ጉዳቶች እንዳይቆጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ጉዳቶች የሚባሉት በሆኑ አደጋዎች ምክንያት የደረሱ እንደ በድንጋይ መፈንከት፣ ወድቆ መሠበር፣ በጩቤ መቀደድ፣ መርዝ መውሰድ ....... ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው እንጂ በሽታዎች /ምሳሌ ወባ፣ ኩፍኝ፣ .....ወዘተ./ በቂ ምግብ አለማግኘት፣ በሥራ ብዛት መድከምና የመሳሰሉትን ሌሎች ችግሮች የሚያጠቃልል መሆኑ ለመልስ ሰጪዎች ግልጽ እንዲሆንላቸው ማድረግ ያስፈልጋል::

አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል የሚባለው በጉዳቱ ምክንያት ቢያንስ ቢያንስ ለአንድ ሙሉ ቀን የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ካልቻለ፣ አደጋው ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕክምና ያደረገ፣ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ሕክምና አስፈልጎት ያጣን ግለሰብ ያጠቃልላል:: ስለዚህ ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ጥናቱ ከሚደረገበት ዕለት በፊት በነበሩት 14 ቀናት ውስጥ ጉዳት ደርሶበት ከነበረ መልሱ "አዎን" ይሆናል፣ በማንኛውም ቀን ጉዳት ካልደረሰበት ግን መልሱ "የለም" ነው:: ግን "አዎን" ወይም "የለም" በማለት ፈንታ እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች መሠረት ነው::

አዎን = 1     የለም = 2

ባለፉት 14 ቀኖች ውስጥ አንድ ሰው ጉዳት ደርሶበት ነበር ሲባል በሆነ አደጋ ምክንያት ጉዳቱ በዚሁ ወቅት የጀመረ የሆነ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ የጀመረ ጉዳት ቢሆንም ባለፉት 14 ቀናት ውስጥም ጥቃት ማድረሱን ከቀጠለ ያው ሰውየው በወቅቱ ጉዳት ላይ እንደነበረ ይቆጠራል::

ዓምድ 21:- አደጋ ደርሶብዎት ከተጎዱ ጉዳቱ ለስንት ቀናት ቆየብዎት?

አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት አንድ ዓይነት ጉዳት ብቻ ከደረሰበት ካለፉት 14 ቀናት ውስጥ ከደረሰበት ጉዳት ሳይድን የቆየበት ቀናት ብዛት በዚህ ዓምድ ይጻፋል:: ባለፉት 14 ቀናት ግለሰቡ ከአንድ በበለጡ ጉዳቶች፣ ከተጠቃ ደግሞ እያንዳንዱ ጉዳት የቆየበት ጊዜ ተደምሮ የቀኑ ብዛት በዓምዱ የመዘገባል:: ግን ከአንድ የበለጡ ጉዳቶች በአንድ ጊዜ ደርሰውበት ለሆነ ቀናት አብረው ቢቆዩ አንድ ጉዳት እንደደረሰበት ተቆጥሮ የቀኑ ብዛት ይመዘገባል:: ሆኖም አንድ ጉዳት ለብቻው ሶስት ቀናት፣ ሌላው ጉዳት ደግሞ ለብቻው 5 ቀናት፣ ሶስተኛው ጉዳት ደግሞ ለብቻው ለአንድ ቀን ቢቆይበት በአጠቃላይ ሶስት ጉዳቶች በአንድነት ለዘጠኝ ቀናት የቆየበት መሆኑ በዓምዱ መገለጽ አለበት:: ይኸውም እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው ቁጥር ባለ ሁለት ዲጂት /አኃዝ/ መሆን ስላለበት ቁጥሩ ከ 10 ያነሰ ከሆነ በስተግራ በኩል "0" በመጨመር ባሉሁለት ዲጂት አድርጎ መጻፍ አለበት:: እዚህም ላይ ማስታወስ የሚገባን በዓምዱ ውስጥ የሚመዘገበው የቀኖች ብዛት ከ14 መብለጥ የለበትም::

ዓምድ 22:- አደጋ ደርሶብዎት ከተጎዱ በጉዳቱ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ?

"የዘወትር ተግባር" የሚለው ትርጉም ቀደም ሲል በዓምድ 19 ሥር የተሰጠ ስለሆነ ግልጽ ነው:: እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው እያንዳንዱ በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በጉዳቱ ወይም በጉዳቶቹ ምክንያት ካለፉት 14 ቀናት ውስጥ የዘወትር ተግባሩን ሊያከናውንባቸው ያልቻለባቸውን ቀናት ብዛት በመደመር ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበት በጉዳቱ ምክንያት መደበኛ ተግባሩን ለማከናወን ባለመቻሉ ለዘጠኝ ቀናት ቢያቋርጥ በዓምዱ "09" የሚል አኃዝ መሥፈር አለበት:: እንደዚሁም ሌላው ሰው ጥናቱ ከተካሄደበት ቀን ጀምር ባለፉት 14 ቀናት በአንድ ጉዳት ምክንያት መደበኛ ተግባሩን ለማከናወን ባለመቻሉ ተግባሩን ለሁለት ቀናት ቢያቋርጥ፣ በሌላ ጉዳት የተነሳ ደግሞ ለሌላ ስድስት ቀናት ተግባሩን ቢያቋርጥ፣ እንደዚሁም በሶስተኛው ጉዳት ምክንያት ለሌላ አራት ቀኖች ተግባሩን ቢያቋርጥ በአንድ ላይ በሶስት ጉዳቶች የተነሳ ይህ ግለሰብ መደበኛ ተግባሩን ለ12 ቀናት ማቋረጡ በዓምዱ ይገለጻል:: ይህም ዓምድ ሲሞላ መገንዘብ

የሚገባን የሚመዘገበው የቀናት ብዛት ከ14 መብለጥ የሌለበት መሆኑን ነው::
እንዲዚሁም የሚመዘገበው ቁጥር ከ10 ያነሰ ከሆነ በስተግራ በኩል "0"
በመጨመር ባለሁለት ዲጂት /አኃዝ/ አድርጎ መጻፍ ያስፈልጋል::

ቁጥር 23:- አደጋ ደርሶብዎት ከተጐዱ ጉዳቱን ያደረሰው ውጫዊ ምክንያት

እዚህ የሚፈለገው ጉዳቱን ያደረሰው ውጫዊ ምክንያት ስለሆነ አብዩና ለረዥም ጊዜ የቆየው ጉዳት የደረሰበትን ምክንያት ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች ትክክለኛውን መርጦ የተሰጠውን ኮድ ብቻ መጻፍ ነው:-

01 = ሳይታሰብ በመውደቅ በደረሰ አደጋ ምክንያት፣
02 = ከጋማ ከብት ላይ በመውደቅ ወይም በሌሎች ከብቶች በመረገጥ ወይም በመወጋት በደረሰ አደጋ ምክንያት

03 = ሳይታሰብ በመቃጠል በደረሰ አደጋ ምክንያት /መቃጠል ሲባል በእሳት ብቻ ሳይሆን በፈላ ውኃ በአሲድ እና በመሳሰሉት ሁሉ ነው/፣

04 = በጦር መሣሪያ በደረሰ ያልታሰበ አደጋ ምክንያት /■ጠብ ወይም በትንኰል ምክንያት የሆነውን አይጨምርም/፣

05 = ሳይታሰብ መርዝ ወይም መርዝ ያለው ነገር በመውሰድ በደረሰ አደጋ ምክንያት ፣

06 = በተሽከርካሪዎች /ለምሳሌ መኪና፣ ደቅደቄ፣ ባቡር ....... ወዘተ/ በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

07 = ከሰው ጋር በመጣላት ወይም ተንኰለኛ ሰው በጣለው በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

08 = በመነከስና በመነደፍ በደረሰ አደጋ ምክንያት:- ለምሳሌ በውሻ፣ በአውሬ፣ በጊንጥ፣ በእባብ፣ .... ወዘተ.
09 = ራስን ለመግደል በመሞከር በደረሰ አደጋ ምክንያት፣
10 = በሌላ ከዚህ በላይ ያልተጠቀሱ አደጋዎች ምክንያት፣

እነዚህም ከላይ የተዘረዘሩት የጉዳት ምክንያቶች ከነ ኮዶቻቸው በዓምዱ አገጀ ይገኛሉ::

<u>ዓምድ 24 – 31:- ባለፉት 14 ቀናት በሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ከደረሰብዎት ለመፈወስ ከሚከተሉት የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? የሕክምና ዕርዳታ ካገኙ ያገኙበት ጊዜ ብዛት</u>:

በተጠቀሰው ወቅት ውስጥ በሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ያጠቃቸው ሰዎች/ለዓምድ 15 ወይም 20 መልሱ "1" ከሆነ/ ለመዳን ሲሉ ያደረጉዋቸው ጥረቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ ይሠፍራሉ:: መጀመሪያ ሰውየው ለመዳን ሲል ከሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ፣ ከቀበሌ ጤና ተጠሪ፣ ከመድኃኒት ቤት፣ ከባሕላዊ ሕክምና አዋቂ፣ ሕክምና ሞያ ከሌለው ጉረቤት፣ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ ወይም ሌላ ሰው የሕክምና ዕርዳታ ለማግኘት ወይም ራሱን በራሱ ለማከም የሞከረ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በመጠየቅና በመሳሰሉት መንገዶች ማጣራት ያስፈልጋል:: ከዚያም የሕክምና እርዳታ ለማግኘት መሞከሩ የተረጋገጠ ከሆነ /ለዓምድ 24 መልሱ "1" ከሆነ/ እርዳታውን ከየት ለማግኘት እንደሞከረና ስንት ጊዜ እንደሞከረ መታወቅ ስላለበት የሕክምና እርዳታ ማግኘት /ለማግኘት መሞከር/ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል::

ለምሳሌ አንድ ሰው ወደ ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ ሄዶ ዶክተር፣ ጤና መኩንን ወይም ነርስ ይመረምረውና መድኃኒት ከማዘዙ በፊት የደም ምርመራ ያዝለታል:: ሰውየው በማግሥቱ ተመልሶ ደሙን ለምርመራ ይሰጣል፣ ከዚያም ከሁለት ቀን በኋላ የደም ምርመራውን ውጤት ይዞ ወደ ሐኪሙ፣ ጤና መኩንኑ፣ ወይም ነርሱ ይመለስና በዚህን ጊዜ መድኃኒት ይታዘዝለታል: እንግዲህ ሰውየው ወደ ሆስፒታሉ ጤና ጣቢያው ወይም ክሊኒኩ የተመላለሰው ሶስት ጊዜ ቢሆንም ዶክተሩን፣ ጤና መኩንኑን ወይም ነርሱን ያየው ሁለት ጊዜ ስለሆነ በሆስፒታሉ፣ በጤና ጣቢያው ወይም በክሊኒኩ የሕክምና ዕርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት እንደ ሁለት ጊዜ /"2"/ ብቻ ይቆጠራል:: ስለዚህ ሰውየው በተጠቀሰው ወቅት ከሆስፒታል፣ ከጤና ጣቢያ ወይም ከክሊኒኩ ያገኘው የሕክምና እርዳታ ይህ ብቻ ከሆነ በዓምድ 25 ውስጥ የሚጻፈው "2" ይሆናል:: ለመጀመሪያ ወደ ሆስፒታሉ፣ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ የሄደ ጊዜ ዶክተሩን፣ ጤና መኩንኑን ወይም ነርሱን አይቶ የሕክምና እርዳታ ካገኘ በዓምዱ "1" ይጻፋል ማለት ነው:: ያገኘው የሕክምና እርዳታ ሰውየውን ካላዳነው ወይም ሁኔታው ከተተለ የሚያስፈልገው ከሆነ ሰውየው ተጨማሪ የሕክምና ዕርዳታ እስኪያገኝ ድረስ እንደገና ወደ ሆስፒታሉ ይመላለስ ይሆናል:: ሁለተኛውን የሕክምና እርዳታ ካገኘ ደግሞ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ታይቶ እርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት ተደምሮ በዓምድ 25 ይሠፍራል::

ይህ ማለት የሚፈለገው ወደ ሆስፒታል፣ የጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ፣ የቀበሌ የጤና ተጠሪ፣ የመድኃኒት ቤት ወይም የባሕላዊ ሕክምና አዋቂ ዘንድ ሄዶ እነርሱን ለሕክምና እርዳታ አይቶ ያናገረባቸው /መድኃኒት ቢያዝለትም፣ ባያዝለትም/ ጊዜ

ብዛት ነው፡፡ ዶክተርን ማየት ሁልጊዜ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘት ስለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ሐኪሙ ሰውየውን ወደ ሌላ ሆስፒታል ወይም ወደ ሌላ ሐኪም እንዲሄድ ሊመክረው ይችላል፤ እንደዚሁም የተፈለገው መድኃኒት በወቅቱ ላይገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ የጤና ባለሙያው /ሃኪሙ፣ ጤና መኮንኑ፣ ነርሱ/ ወደ ሌላ ጤና ባለሙያ በሽተኛውን ቢመራው፣ ወይም መድኃኒት አዘለት መድኃኒቱ ሳይገኝ ቢቀር እንደዚሁም ሌሎች የመሳሰሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ውሳኔ ወይም መልስ የተሰጠባቸው ስለሆነ በሚመለከተው ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው "1" መሆን አለበት፡፡

ስለዚህ ከህመሙ ወይም በአደጋ ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ለመፈወስ የሕክምና ዕርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት የሚጻፈው ሰውየው ዕርዳታውን ያገኘው ከሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ፣ ከቀበሌ ጤና ተጠሪ፣ ከመድኃኒት ቤት፣ ከባሕላዊ አከሚ አከሚ፣ ባሕላዊ/ካልሆኑ፣ ከራሱ ወይም ከሌላም ጭምር መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

## ዓምድ 24፡- የሕክምና ዕርዳታ አገኘ/ባለፈት 14 ቀናት/?

ማንኛውም የቤተሰቡ አባል በተጠቀሰው ወቅት ውስጥ ከማንኛውም ቦታ ከሕመሙ ወይም በአደጋ ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ለመፈወስ የሕክምና ዕርዳታ ካገኘ መልሱ "አዎን" ካላገኘ ደግሞ "የለም" ስለሆነ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ተስማሚውን ኮድ መጻፍ ነው፡፡

1 = አዎን      2 = የለም

እዚህ ላይ የሕክምና ዕርዳታ አግኝተዋል? ብሎ መጠየቅ በቂ አይሆንም፡ ከሐኪም ቤት ወይም ከጤና ጣቢያ ወይም ከክሊኒክ ባለፈት 14 ቀናት የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? ከዚያም መልሱ "የለም" ከሆነ ከቀበሌ ጤና ተጠሪስ? ከመድኃኒት ቤትስ? ከባሕላዊ አከሚስ/ወጌሻ፣ ቀጠል በጣሽ፣ .... ወዘተ/? አከሚ ካልሆነ ሰውስ? ለዚህ ሁሉ መልሱ "የለም" ከሆነ ራስዎን አከሙ? ወይስ በሌላ ሁኔታ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? በመጨረሻም ለዚህ ሁሉ መልሱ "የለም" ከሆነ "ከአዋቂ" የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? ..... እያሉ በመጠየቅ ማጣራት ነው፡፡

ዓምድ 25:- ከሆስፒታል፣ የጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ የሕክምና ዕርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/?

በዓምድ 24 መልሱ አዎን /"1"/ ከሆነ/. ሰውየው ከሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ የሕክምና ዕርዳታ ያገኘ ከሆነ እርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት በዓምድ 25 ውስጥ ይጻፋል::

ዓምድ 26:- ከቀበሌ ጤና ተጠሪ የሕክምና ዕርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/?

በዓምድ 24 መልሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውየው ከቀበሌ ጤና ተጠሪ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ የሕክምና ዕርዳታ ካገኘ ዕርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት በዓምድ 26 ውስጥ ይጻፋል::

ዓምድ 27:- ከመድኃኒት ቤት /ከፋርማሲ/ የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/?

ግለሰቡ ባለፉት 14 ቀናት ታሞ ወይም በአደጋ-ምክንያት ጉዳት ደርሶበት ለመፈወስ እርዳታ ማግኘቱን በዓምድ 24 ከገለጸ ከመድኃኒት ቤት ወይም ከፋርማሲ የሕክምና እርዳታ ማግኘቱን ጠይቆ ለስንት ጊዜ ከመድኃኒት ቤት ወይም ከፋርማሲ እርዳታ እንዳገኘ በዓምዱ ይሠፍራል::

ዓምድ 28:- ከባሕላዊ አካሚ የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/?

ባሕላዊ አካሚ የሚባሉት እንደ ቀጠል ባጣሽ፣ መድኃኒት በግለጨማቂ ወይም ቀማሚ፣ ወጌሻ፣ አዋቂ፣ .... ወዘተ. የመሳሰሉት ችሎታቸውን ያገኙት በዘመናዊ በተመሠረተ ትምህርትና ሥልጠና ሳይሆን በራሳቸው ልምምድ ከማድረግና ከባሕል ሕክምና አዋቂዎች ያገኙት ዕውቀት የሆነ እንደሆነ ነው:: በጠበል መጠቀም እንደዚሁ ከባሕላዊ አካሚ የሕክምና ዕርዳታ እንደማግኘት ይቆጠራል:: ከአዋቂ የሕክምና እርዳታ አግኝተዋል ወይ ብሎ ከመጠየቅ በሚቻል መጠን መቆጠብ ያስፈልጋል:: በመጨረሻ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሌሎች ጥያቄዎች ተጠይቀው ካለቀ በኋላ ብቻ ከአዋቂ የሕክምና እርዳታ ማግኘታቸውን መጠየቅ ያስፈልጋል::

ስለዚህ በዓምድ 24 መልሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውየው ከባሕላዊ አካሚ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ የሕክምና እርዳታ ያገኘ ከሆነ እርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት በዓምድ 28 ውስጥ መጻፍ አለበት::

## ዓምድ 29:- አካሚ ካልሆኑ ሰዎች የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት /ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ/?

በአርእስቱ እንደተመለከተው አካሚ ያልሆኑ ሰዎች የተባሉት በቂ ዕውቀት ወይ ለምድ ኖሮአቸው ሳይሆን የሚያቁት ሰው በችግር ላይ ስለሆነ በስሜትና እና ውቀዋለን በሚሉት መድኃኒት ለጊዜውም ቢሆን የሚረዱ ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ በዓም ድ 24 መለሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውየው ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሕክምና ዕርዳታ ያገኘ ከሆነ ዕርዳታ ያገኘበት ጊዜ ብዛት በዓምድ 29 ይመዝገብ.:

## ዓምድ 30:- እራሳቸውን አከሙ? /ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ ራሳቸውን ያከሙበት ጊዜ ብዛት/.

በሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በቂ የሕክምና ዕውቀትና ለምድ ሳይኖረው ቀደም ሲል በሰማው መሠረት ያድነኛል ብሎ ያመነውን መድኃኒት ገዝቶ፣ ቀጠል በጥሶ፣ ሥር ነቅሎ፣ ወይም ቀምሞ ..... ወዘተ. ማንም ሳያዝለት የሚወስድበት ጊዜም ሊኖር ይችላል:: ስለዚህ በዓምድ 24 ውስጥ መለሱ አዎን /"1"/ ሆኖ አንድ አካሚ ያልሆነ ሰው ለራሱ ሕክምና ካደረገ በዓምድ 30 ውስጥ ለራሱ በራሱ ሕክምና ያደረገበት ጊዜ ብዛት ይገለጻል::

## ዓምድ 31:- ከሌላ /ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ ከሌላ የሕክምና እርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት/?

በዓምድ 24 ውስጥ ያለው መልስ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውየው ባለፈት 14 ቀናት ውስጥ ሕመም ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበት ለመፈወስ ከዓምድ 25 እስከ 30 ከተጠቀሱት የሕክምና እርዳታ ማግኛ ዘዴዎች በተለዩ ሁኔታዎች የሕክምና እርዳታ ካገኘ የጊዜው ብዛት በዓምድ 31 ውስጥ ይገለጽ:: ለምሳሌ አንድ ሰው በአካባቢው ከሚገኝ የተረጋገጠ የሕክምና ሙያ የሌለው "መርፌ"ወጊ" በዚህ ወቅት አራት ጊዜ የ ክምና እርዳታ ካገኘ በዚህ ዓምድ ውስጥ "4" መጻፍ አለበት::

## ዓምድ 32:- በዓምድ 25 እና 26 መሠረት የሕክምና እርዳታ ካላገኙ ምክንያት?

በዓምድ 25 የተጠቀሱት የሕክምና እርዳታ ማግኛ ዘዴዎች ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ ሲሆኑ በዓምድ 26 ደግሞ የቀበሌ የጤና ተጠሪ ነው:: ስለዚህ አንድ የቤተሰብ አባል ባለፈት 14 ቀናት ታሞ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበት የሕክምና እርዳታ ለማግኘት መሞከሩ በመረጋገጡ በዓምድ 24 ውስጥ የተሰጠው መልስ አዎን /"1"/ ሆኖ ዓምዶች 27፣ 28፣ 29፣ 30 እና 31 የሰፈሩ መልሶች ቢኖሩም በዓምዶች 25 እና 26 ምንም ቁጥር ወይም አኃዝ ካልገባ ሰውየው

ከሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ ወይም ቀበሌ ጤና ተጠሪ ምንም የሕክምና ዕርዳታ አላገኘም ማለት ነው:: ስለዚህ አባሉ ከሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ ወይም ከቀበሌ ጤና ተጠሪ የሕክምና እርዳታ ያላገኘበት ምክንያት መታወቅ ስላለበት በዓምዱ አግርጌ ከተሰጡት ምክንያቶች ትክክለኛውን መርጦ የአንዱን ኮድ በዚህ ዓምድ ውስጥ ማስገባት ነው:: ሊኖሩ የሚችሉ ምክንያቶችም ከነኮዳቸው ቀጥሎ ተዘርዝረዋል:—

1 = በጣም ስለራቀ፣ /ሆስፒታሉ፣ ጤና ጣቢያው፣ ክሊኒኩ ወይም የቀበሌው ጤና ተጠሪው የሚገኝበት ሥፍራ በጣም ስለራቀ/
2 = በቂ ገንዘብ ስለሌለኝ /ወጪው ስለሚበዛብኝ/
3 = ባሕላዊ መድኃኒት፣ ስለወሰድኩ
4 = ይጠቀማል /ይረዳኛል፣ ያድነኛል/ ብዬ ስላላመንኩ፣
5 = ይተወኛል በማለት
6 = ለሕክምና ወረፋ ስለማይደርሰኝ
7 = የሚያስፈልገውን መድኃኒት አገኛለሁ ብዬ ስለማላገምት
8 = ሌላ /ከ 1 እስከ 7 ከተዘረዘሩት የተለየ ማንኛውም ምክንያት/::

መልስ ሰጭዎች ምክንያት ከመስጠት በጣም ከተቆጠቡ እነዚህን ምክንያቶች አንድ ባንድ በመዘርዘር ማስመረጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 33:— አብዛኛውን ጊዜ የት ነው የሚፀዳዱት /ዕዳሪ የሚወጡት/?

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የት እንደሚፀዳዳ /ዕዳሪ እንደሚወጣ/ በማጣራት በዓምዱ አግርጌ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መርጦ ኮዱን መጻፍ ያስፈልጋል:: የተሰጡት አማራጮችም ከነኮዳቸው የሚከተሉት ናቸው —

1 = ከቤቶች አካባቢ ራቅ ባለ ቦታ
2 = ከጋር ወይም ከገቢ ውስጥ
3 = በሽንት ቤት /በመፀዳጃ ጉድጓድ/
4 = ሌላ /ማለት ከመጀመሪያዎቹ ሶስት በተለየ ቦታ/

እንደ ሕፃን፣ በሽተኛ ወይም ጉዳት የደረሰበት በው፣ አካለ ስንኩል የመሳሰሉ አባላት ሽንት ቤት ሄደው ለመቀመጥ ባይችሉም ሽንታቸው /ዓይነ ምድራቸውን/ ሁልጊዜ ሽንት ቤት /መፀዳጃ ጉድጓድ/ ውስጥ የሚደፋ ከሆነ በሽንት ቤት ውስጥ እንደሚፀዳዱ /እዳሪ እንደሚወጡ/ ይቆጠራል፣ እንዲሁ ጋር እሚጣል ከሆነ ግን ጋር እንደሚፀዳዱ መቁጠር አለበት::

በተጨማሪም አባሎቹ በሽንት ቤት /መጸዳጃ ጉድጓድ/ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ለማጣራት ሽንት ቤቱን /መጸዳጃ ጉድጓዱን/ ማየት አስፈላጊ ነው::

## ዓምድ 34 እና 35:- ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ብቻ

ዕድሜአቸው 10 ዓመት ወይም በላይ የሆኑ ሴቶች የቤተሰብ አባላት ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ መውለዳቸው ወይም አለመውለዳቸውና ከወለዱ ደግሞ ማን እንዳዋለዳቸው በነዚህ ሁለት ዓምዶች ውስጥ ይመለከታል::

## ዓምድ 34:- ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ወልደዋል?

ዕድሜአቸው 10 ዓመት ወይም በላይ የሆኑ ሴቶች ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ልጅ ወልደው እንደሆነ ተጠይቀው መልሱ ከዚህ በታች በተመለከተው ኮድ መሠረት እዚህ ዓምድ ውስጥ ይጻፋል:-

1 = አዎን 2 = የለም

አማራጭ መልሶቹ ከነኮዶቻቸው በዓምዱ ራስጌ ተሰጥተዋል:: ምናልባት አንዳንድ ሴቶች ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ልጆች ወልደው ልጆቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሞቱ ወልደናል ላይሉ ስለሚችሉ ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ልጅ ወልደው አልሞተብያትም ብሎ በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል::

## ዓምድ 35:- ለዓምድ 34 መልሱ "አዎን" ከሆነ ማን አዋለዶት?

ባለፉት 2 ዓመት ልጅ መውለዳቸው ለተረጋገጠ /በዓምድ 34 መልሱ "1" ከሆነ/ ሴቶች ማን እንዳዋለዳቸው ጠይቆ በማጣራት መልሱ እዚህ ዓምድ ውስጥ መጻፍ አለበት:: መልሱም በዓምዱ አግርጌ ከተመለከቱት አማራጮች አንዱ ብቻ መሆን ስላለበት ትክክለኛውን መልስ መርጦ ኮዱን ብቻ በዚህ ዓምድ ውስጥ መጻፍ ያስፈልጋል:: አማራጭ የሆኑት መልሶች ከነኮዶቻቸውም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

1 = የጤና ባለሙያ /ሴትየዋ ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ድረስ በመሄድ ወይም ባለሙያው ቤታቸው ድረስ መጥተው ሲያዋልዷቸው)
2 = የቀበሌ የጤና ተጠሪ፣
3 = ባሕላዊ አዋላጅ፣
4 = የማዋልድ ሙያ የሌላቸው ሰው

5. = ማንም አላዋለደኝም /ራሴን አዋለድኩ/፤

**ዓምድ 36:- ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ አብዛኛውን ጊዜ የሚያገኘው ከየት ነው?**

ቤተሰቡ ለመጠጥና ለምግብ ማዘጋጃ የሚሆነውን ውኃ የሚያገኘው ከጉድጓድ፤ ከምንጭ፣ ከወንዝ፤ ከኩሬ፤ ከሐይቅ /ኩሬ/፤ ወይም ከነዚህ ከተለዩ ቦታ ሊሆን ይችላል:: አንድ ቤተሰብ ውኃ ከኩሬ ያገኛል የሚባለው ራቅ ብሎ ከሚገኝ ምንጭ፣ ሐይቅ፤ ኩሬ፤ ወይም ወንዝ በኩሬ /የበረት ኩሬ/ አማካይነት በመጣ ውኃ የተ ጠቀመ እንደሆነ ነው:: ስለዚህ ቤተሰቡ ለመጠጥና ለምግብ ማብሰያ የሚሆነውን ውሃ ከምን እንደሚያገኝ በመጠየቅ ከተዘረዘሩት አማራጮች ትክክለኛውን በመምረጥ በሚመለከተው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት ይጻፋል::

1 = ጉድጓድ ☐ 2 = ምንጭ ☐ 3 = ወንዝ ☐

4 = ኩሬ ☐ 5 = ሐይቅ ☐ 6 = ሌላ ☐

**ዓምድ 37:- ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው ለጤንነት አመቺ በሆነ መንገድ በተጠበቀ ውኃ ነው?**

ሰዎች ጸዳት በደንብ ባልተጠበቀ ውኃ ስለሚጠቀሙ በሽታ እንደሚይዛቸው የታወቀ ነው:: ስለሆነም በምንጠቀመው ውኃ ምክንያት በሽታ እንዳይደርስብን ለመጠ ጥና ለምግብ ማዘጋጃ የምንጠቀምበት ውኃ የበሽታ ምንጭ በማይሆንበት መንገድ ለጤ ንነት ተስማሚ እንዲሆን አድርጎ መጠበቅ ያስፈልጋል:: ዓምድ 35 ውስጥ ቤተሰቡ የሚጠ ውኃ አብዛኛውን ጊዜ ከየት እንደሚያገኝ ተመልክተናል:: እንግዲህ ቤተሰቡ የሚጠ ቀመው በተጠበቀ ውኃ ነው ለማለት የሚቻለው ውኃው እዚያው እሚገኝበት ቦታ ላይ የበሽታ ምንጭ በማይሆንበት መንገድ የተጠበቀ እንደሆነ ነው::

በአሁኑ ወቅት በገጠር ኢትዮጵያ ባሉት ብዙ ሁኔታዎች የውኃ አጠባበቅ ዘዴዎች በብዙ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ይለያያሉ:: የጉድጓድና የምንጭ ውኃ አጠባበቅ ዘዴዎች በብዛት ተመሳሳይ ስለሆኑ የሁለቱም አጠባበቅ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል::

1/ በጉድጓድ ወይም በምንጩ ዙሪያ በሲሚንቶ የተገነባ ግንብ መኖር አለበት፤ ይኸውም—

ሀ/ ጉድጓድ ከሆነ እንደሚገኝበት አፈር ሁኔታ ግንቡ ቢያንስ ከ 2 እስከ 4 ሜትር ውስጥ የገባ እና 70 ሳንቲ ሜትር ያህል ደግሞ ከመሬት የወጣ መሆን ይኖርበታል፤

1/ ምንጭ ከሆነ ግንቡ ዓለት እስኪገኝበት ድረስ መሬት ውስጥ የገባና እንደ አስፈላጊነቱ ከመሬት በላይ ከፍብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል ፡ ከግንቡ በአንዱ በኩል ውኃ ማውጫ ክፍት ቧንቧ ያለው መሆን አለበት።

2/ በጉድጓድም ሆነ በምንጭ ዙሪያ የተገነባው ግንብ ከላይ ከሲሚንቶ የተሠራ ወይም ሌላ ዓይነት ጥብቅ ክዳን እንዲኖረው ያስፈልጋል።

3/ ወደ ጉድጓዱ ወይም ምንጩ ጎርፍ እንዳይገባ አቀጣጫውን የሚቀይር ተስማሚ ቦይ ጎርፍ ሊመጣ ከሚችልበት አካባቢ ወይም አቅጣጫ መኖር አለበት።

4/ እንደ ሠገራ ቤት ከመሳሰሉ ውኃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ጉድጓዱም ሆነ ምንጩ ቢያንስ ቢያንስ ከ 25 እስከ 30 ሜትር የራቀ መሆን አለበት።

5/ እንደዚሁ ዓይነት በካይ ቆሻሻ ከሆኑ ነገሮች ለምሳሌ የሠገራ ጉድጓድ የውሃው ጉድጓድ ወይም ምንጩ ከሚገኝበት ከፍ ባለ ቦታ ቢኖሩ ርቀታቸው በተራ ቁጥር 4 ላይ ከተጠቀሰው ርቀት ብዙ መብለጥ ይኖርበታል።

ስለዚህ ቤተሰቡ ውኃ የሚያገኘው ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች አንዱም ሳይቀር በሙሉ በሚያሟላ ሁኔታ ከሚጠበቅ ጉድጓድ ወይም ምንጭ ከሆነ ከተጠበቀ ውኃ እንደተጠቀመ ይቆጠራል። በቧንቧ የሚመጣ ውሀ ካልሆነ በስተቀር ከወንዝ ወይም ከሐይቅ እየተቀዳ የሚገኘው ውኃ በአጠቃላይ ያልተጠበቀ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ከወንዝ ወይም ከሐይቅ እየቀዳ የሚጠቀም ቤተሰብ በተጠበቀ ውኃ አይጠቀምም ማለት ነው።

ከቧንቧ የሚገኝ ውኃም የተጠበቀ ነው የሚባለው ከቧንቧው መነሻ ላይ ያለው ውኃ የተጠበቀ እንደሆነ ነው። ስለዚህ አንድ ቤተሰብ ውኃ የሚያገኘው ከቧንቧ ከሆነ የቧንቧው ውኃ የሚመጣው ከተጠበቀ ውኃ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ጠንቅቆ ማጣራት ያስፈልጋል። የቧንቧው ውኃ የሚመጣው ከጉድጓድ ወይም ከምንጭ ከሆነ የተጠበቀ ውኃ ነው ለማለት የሚቻለው ጉድጓዱ ወይም ምንጩ ከፍ ብሎ በተዘረዘረው ሁኔታ የተጠበቀ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው።

ከወንዝ ወይም ከሐይቅ የሚመጣ የቧንቧ ውኃ የተጠበቀ ነው የሚባለው ቧንቧው አሚነሳበት ቦታ ውኃው ከሎሪንና በመሳሰሉት ኬሚካሎች በሳይንሳዊ መንገድ የተጣራ እንደሆነ ብቻ ነው።

ስለዚህ ቤተሰቡ በተጠበቀ ውኃ የሚጠቀም ከሆነ "አዎን" ከሚለው ቀጥሉ ባለው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት ማስገባት ያስፈልጋል:: ነገር ግን ቤተሰቡ ባልተጠበቀ ውኃ የሚጠቀም ከሆነ "የለም" በሚለው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት ማስገባት ያስፈልጋል::

1 = አለው ☐      2 = የለም ☐

ዓምድ 38:— ቤተሰቡ ቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ አለው?

የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ የሚባለው እንደ የቤት ጥራጊ፣ ቅጠላ ቅጠል፣ የብርቱካን ወይም የሙዝ ልጣጭ .... ወዘተ. የመሳሰሉትና ሌሎች ዓይነቶች የቤት ጠጣር ቆሻሻዎች የሚጣልበት ወደ መሬት ውስጥ በቂ ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ነው:: ጉድጓዱ ለቤተሰቡ ብቻ ወይም ከሌሎች ቤተሰቦች በጋራ የሚጠቀምበት ሊሆን ይችላል:: የአዛባ ወይም የአበት ጉድጓድ እንደ ቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ የማይቆጠር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ስለዚህ ቤተሰቡ የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ ካለው "አዎን" ከሚለው ቀጥሉ ባለው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል:: ቤተሰቡ የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ ከሌለው ደግሞ "የለውም" በሚለው ቀጥሉ ባለው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል::

1 = አዎን ☐      2 = የለውም ☐

ቤተሰቡ የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ ያለው መሆኑንም አይቶ ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው::

ዓምድ 39.— ቤተሰቡ የሚጠቀምበት መፀዳጃ ጉድጓድ አለው?

የመፀዳጃ ጉድጓድ የቤተሰቡ አባላት እንዲፀዳዱበት /ዐዳሪ እንዲወጡበት/ በቂ ጥልቀትና መክደኛ ኖሮት የተዘጋጀ ጉድጓድ ሲሆን ጣራ ባለው ግድግዳ ወይም አጥር የተከበበ ሊሆንም ይችላል:: ጉድጓዱም ቤተሰቡ ብቻ የሚጠቀምበት ወይም ቤተሰቡ ከሌሎች ጎረቤት ቤተሰቦች ጋር በጋራ የሚጠቀምበት ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ቤተሰቡ የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ጉድጓድ መኖሩን በመጠየቅ የመፀዳጃ ጉድጓድ ካለው "አዎን" በሚለው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት አስፍር:: ነገር ግን ቤተሰቡ የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ጉድጓድ ከሌለው "የለውም" በሚለው ሳጥን የ "x" ምልክት

በዓምዱ ይገባል:-

1 = አዎን ☐    2 = የለውም ☐

ቤተሰቡ የመፀዳጃ ጉድጓድ አለን ካለ አይቶ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

**ዓምድ 40:- የቤተሰቡ አባላት ከሚያድሩበት ቤት የቤት እንስሳት ያድራሉ?**

በአንዳንድ አካባቢዎች እንደ ደሮ፣ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ ..... ወዘተ. የመሳሰሉት የቤት እንስሳት የቤተሰቡ አባላት በሚያድሩበት አንድ ክፍል ብቻ ባለው ቤት ወይም ብዙ ክፍሎች ባሉት ቤት ሰዎች በሚያድሩበት ክፍል ውስጥ የቤት እንስሳት አብረው አንድ ቀግ ተሰጥቶአቸው ያድራሉ:: ስለዚህ እንስሳት ከቤተሰቡ አባላት ጋር አንድ ቤት ወይም ክፍል ውስጥ የሚያድሩ ከሆነ "አዎን" ከሚለው ቀጥሎ ባለው ሳጥን ውስጥ የ "x" ምልክት መጻፍ ያስፈልጋል:: ነገር ግን የቤተሰቡ አባላት የቤት እንስሳት ከሚያድሩበት ቤት ወይም ክፍል ሌላ ቦታ /በረት/ የሚያድሩ ከሆነ "የለም" በሚለው ሳጥን ውስጥ የ"x" ምልክት መጻፍ አለበት::

1 = አዎን ☐    2 = የለም ☐

እንስሳት ቤት ውስጥ ከአባላት ጋር በአንድነት የሚያድሩ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ከመጠየቅ አልፎ ካስፈለገ ቤት ውስጥ ገብቶ ሁኔታውን /አበት፣ በጠጥ፣ ፋንድያ ..... መኖሩን፣ ሽታውን/ ማየት ያስፈልጋል:: ሆኖም እንስሳት ሲባል እንደ ድመትና ውሻ ያሉትን የቤት እንስሳት አያጠቃልልም::

በተጨማሪም እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የጥያቄው ዓላማ የቤት እንስሳት የቤተሰቡ አባላት ከሚያድሩበት ቤት /ክፍል/ ውስጥ አብረው ማደራቸውን ለማወቅ እንጅ ቤተሰቡ የቤት እንስሳት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ለማወቅ አይደለም:: ስለሆነም ይህ ጥያቄ ለቤተሰቡ ሲቀርብ የቤት እንስሳ አላችሁ ወይ? ብሎ መጀመሩ ለቤተሰቡ የከብት ቆጠራ ስለሚመስለና ቤተሰቡም ብዙውን ጊዜ ከብት "የለንም" የሚል መልስ የሚሰጥ መሆኑ ተደርሶበታል:: ስለዚህ ጥያቄውን ቢቀጥታ የቤት እንስሳት ከቤተሰቡ አባላት ከሚያድሩበት ቤት/ክፍል/ውስጥ አብረው ያድራሉ ወይ ብሎ መጠየቅ ነው እንጂ የቤት እንስሳት አላችሁ ወይ ብሎ መጀመሩ የተከለከለ ነው::

የመረጃ ሰብሳቢው፣ የመስክ ተቆጣጣሪውና የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ኃላፊ ስምና ፊርማ:-

በዚህ ሥፍራ መረጃ ሰብሳቢው፣ የመስክ ተቆጣጣሪውና የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ኃላፊ ጥናቱ በትክክል መከናወኑን ለማረጋገጥ ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና እንደዚሁም ቀን የሚሰፍርበት ነው:: ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢዎች ሥራው በትክክል መሠራቱን ለማረጋገጥ ለያንዳንዱ ቤተሰብ ፎርሙን ከሞሉ በኋላ ስም ፊርማና ቀን ማስፈር እንዲያመለክቱ ያስፈልጋል:: እንደዚሁም የመስክ ተቆጣጣሪዎች መረጃው በተሰጠው መመሪያ መሠረት መሰብሰቡን አይተው ማረጋገጫቸውን ለማመልከት ስማቸውን በመጻፍ፣ ፊርማቸውንም ማስፈር ይህም ተግባር የተከናወነበትን ቀን እንዲመዘግቡ ያስፈልጋል:: በመጨረሻም የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ኃላፊ መረጃ ሰብሳቢውም ሆነ የመስክ ተቆጣጣሪው ሥራቸውን በትክክል ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ ስሙን፣ ፊርማውንና ቀኑን ማስፈር አለበት::

========================

## የቤተሰብ አባሎች ዕድሜአቸውን እንዲያስታውሱ የሚረዱ የሚታወሱ ታሪካዊ ክንውኖች የተፈጸሙባቸው ቀኖች /ዓመተ ምሕረት ከነወሩ/ እና ክንውኖቹ ከተፈጸሙ እስከ ነሐሴ 1974 ዓ.ም እና የካቲት 1975 ዓ.ም ድረስ ያለፉት ዓመታት

| የሚታወሱ ክንውኖች | ክንውኑ የተፈጸመበት ዓ.ም ከነወሩ | ክንውኑ ከተፈጸመበት ጊዜ እስከ | |
|---|---|---|---|
| | | ነሐሴ 1974 ዓ.ም ያሉት ዓመታት ብዛት | ጥር መጨረሻ የካቲት መጀመሪያ 1975 ዓ.ም አካባቢ ያሉት ዓመታት ብዛት |
| 1. አፄ ዮሐንስ አረፉ /የመተማ ጦርነት/ | መጋቢት 1881 | 93 | 93 |
| 2. አፄ ምኒልክ ነገሡ | ጥቅምት 1882 | 92 | 93 |
| 3. ዘዋይ የተመታበት | 1886 | 88 | 89 |
| 4. የወላሞ ዘመቻ | 1887 | 87 | 88 |
| 5. የአድዋ ዘመቻ | የካቲት 1888 | 86 | 87 |
| 6. አጼ ምኒልክ አረፉ /ልጅ እያሱ ነገሡ/ | ታሕሣሥ 1906 | 68 | 69 |
| 7. ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ነገሡ | መስከረም 1909 | 65 | 66 |
| 8. የሠገሌ ጦርነት | ጥቅምት 1909 | 65 | 66 |
| 9. እቴጌ ጣይቱ አረፉ | 1910 | 64 | 65 |
| 10. የሕዳር በሽታ | ሕዳር 1911 | 63 | 64 |
| 11. ልጅ እያሱ የተያዙበት | ሚያዝያ 1913 | 61 | 61 |
| 12. ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ አረፉ/አቡነ ማቴዎስ አረፉ/ | 1919 | 55 | 56 |
| 13. የማይጨው ጦርነት | መጋቢት 1928 | 46 | 46 |
| 14. የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | የካቲት 1929 | 45 | 46 |
| 15. እንግሊዝ ኢጣልያንን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዘመን | መጋቢት 1933 | 41 | 41 |
| 16. ጣልያን ድል የተመታበት ዓመት | መጋቢት 1933 | 41 | 41 |
| 17. ኤርትራ ከኢትዮጵያ በፌዴሬሽን የተዋሐደችበት ዘመን | መስከረም 1943 | 31 | 32 |
| 18. አቡነ ባስሊዮስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት ዘመን | 1943 | 31 | 32 |
| 19. የሸንቁጤ ረሃብ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን | 1950 | 24 | 25 |

| የሚታወሱ ክንውኖች | ክንውኑ የተፈጸመበት ዓ.ም ከነወሩ | ክንውኑ ከተፈጸመበት ጊዜ እስከ | |
|---|---|---|---|
| | | ነሐሴ 1974 ዓ.ም ያሉት ዓመታት ብዛት | ጥር መጨረሻ የካቲት መጀመሪያ 1975 ዓ.ም አካባቢ ያሉት ዓመታት ብዛት |
| 20. እንጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመፈንቀል ሙከራ ያደረጉበት ዘመን | ታህሣሥ 1953 | 21 | 22 |
| 21. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተዋሐደች | መስከረም1955 | 19 | 20 |
| 22. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቋቋመ | ግንቦት 1955 | 19 | 19 |
| 23. የየካቲት አብዮት የፈነዳበት ጊዜ | የካቲት 1966 | 8 | 9 |
| 24. የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን መውረድ | መስከረም1967 | 7 | 8 |
| 25. የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | የካቲት 1967 | 7 | 8 |
| 26. የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | ሐምሌ 1967 | 7 | 7 |
| 27. የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዕረፍት | ነሐሴ 1967 | 7 | 7 |

| ጥብቅ ምስጢር |
|---|
| ለእስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ |

# የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት
## በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም — የገጠር የጤና ጥናት
## 1974/75

| የጥናቱ መለያ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ |
|---|---|---|---|---|
| | 2 | 0 | 4 | |

| 1- ክፍለ ሀገር | 4 | 5 | 2- አውራጃ | 6 | 7 | 3- ወረዳ | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | |

| 4- ገ/ማሕበር ስም | 10 | 11 | 12 | 5- የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር | 13 | 14 | 15 | 16 | 6- የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር | 17 | 18 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | |

| 7- የቤተሰብ ምድብ | 19 | 8- የጥናቱ ዙር | 20 | 9- ወርና ዓ.ም | 21 | 22 | 23 | 24 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | |

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| መረጃ ሰብሳቢ | | | / / |
| የመስክ ተቆጣጣሪ | | | / / |
| የክፍለ ሀገር እስታቲስቲክስ ኃላፊ | | | / / |

## ክፍል 2 — የቤተሰብ የጤና ሁኔታ

ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች (ዓምድ 15–19); ለዓምድ 15 መልሱ "1" ከሆነ በሽታው ምን ነበር ወይም በሽታዎቹ ምን ምን ነበሩ? (ዓምድ 16–17)

በአደጋዎች ምክንያት · ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ ጉዳቶች (ዓምድ 20–23)

ባለፉት 14 ቀናት በሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ከደረሰብዎት ለመፈወስ ከሚከተሉት (ዓምድ 24–31); ለዓምድ 24 መልሱ "1" ከሆነ የሕክምና ዕርዳታ ያገኙበት ጊዜ ብዛት (ዓምድ 25–31)

ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ብቻ (ዓምድ 34–35)

| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | 32 | 33 | 34 | 35 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተራ ቁጥር | መደበኛ የቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም | ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና | ፆታ 1= ወንድ 2= ሴት | ዕድሜ በሙሉ ዓመት | በሽታ ደርሶባቸው ነበር? 1= አዎን 2= የለም | አንደኛ በሽታ | ሁለተኛ በሽታ | በሽታው ለስንት ቀናት ቆየባቸው? | በበሽታው ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ? | በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎት ነበር? 1= አዎን 2= የለም | አደጋ ደርሶብዎት ከሆነ ጉዳቱ ለስንት ቀናት ቆየብዎት? | አደጋ ደርሶብዎት ከሆነ በጉዳቱ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ? | አደጋ ደርሶብዎት ከሆነ የጉዳቱ ምክንያት ምን ነበር? | የሕክምና ዕርዳታ አግኝተዋል? 1=አዎን 2=የለም | ከሆስፒታል/ጤና ጣቢያ/ክሊኒክ | ከቀበሌ ጤና ተጠሪ | ከመድኃኒት ቤት | ከባሕላዊ አካሚ | አካሚ ካልሆኑ ሰዎች | እራሳቸውን አከሙ | ከሌላ | በዓምድ 25 እና 26 መሠረት የሕክምና ዕርዳታ ካላገኙ ምክንያቱ? | አብዛኛውን ጊዜ የት ነው የሚታከሙት? | ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ወልደዋል? 1= አዎን 2= የለም | ለዓምድ 34 መልሱ አዎን ከሆነ ማን አዋለደዎት? |
| 25 26 | | 27 | 28 | 29 30 | 31 | 32 33 | 34 35 | 36 37 | 38 39 | 40 | 41 42 | 43 44 | 45 46 | 47 | 48 | 49 | 50 | 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 |
| 01 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 02 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 03 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 04 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 05 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 06 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 07 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 08 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 09 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

36 [59] ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውሃ አብዛኛውን ጊዜ የሚያገኘው ከየት ነው ?

1- ጉድጓድ ☐ 2 - ምንጭ ☐ 3 - ወንዝ ☐
4 - ቧንቧ ☐ 5- ሐይቅ ☐ 6 - ሌላ ☐

37 [60] ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው ለጤንነት አመቺ በሆነ መንገድ በተጠበቀ ውሃ ነው ?

1- አዎን ☐ 2- የለም ☐

38 [61] ቤተሰቡ ቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ አለው ?

1- አዎን ☐ 2- የለም ☐

39 [62] ቤተሰቡ የሚጠቀምበት መፀዳጃ ጉድጓድ አለው ?

1- አለው ☐ 2 የለውም ☐

40 [63] የቤተሰቡ አባላት ከሚያድሩበት ቤት የቤት እንስሳት ያድራሉ ?

1- አዎን ☐ 2- የለም ☐

01= ሳይታሰብ በመውደቅ በደረሰ አደጋ ምክንያት
02= ከጋማ ከብት ላይ በመውደቅ ወይም በሌሎች ከብቶች በመረገጥ ወይም በመወጋት በደረሰ አደጋ ምክንያት
03= ሳይታሰብ በመቃጠል በደረሰ አደጋ ምክንያት
04= በጦር መሣሪያ በደረሰ ያልታሰበ አደጋ ምክንያት
05= ሳይታሰብ መርዝ ያለው ነገር በመውሰድ የደረሰ አደጋ
06= በተሽከርካሪዎች በደረሰ አደጋ
07= ከሰው በመጣላት ወይም በተንኮለኛ ሰው ምክንያት የደረሰ አደጋ
08= በመነከስ / በመነደፍ በደረሰ አደጋ ምክንያት
09= ራስን ለመግደል በመሞከር በደረሰ አደጋ ምክንያት
10= በሌላ ምክንያት በደረሰ አደጋ

1= በጣም ስለራቀ
2= በቂ ገንዘብ ስለሌለኝ
3= ባሕላዊ መድኃኒት ስለወሰድሁ
4= ይጠቅማል ብዬ ስላላመንሁ
5= ይተወኛል በማለት
6= ለሕክምና ወረፋ ስለማይደርሰኝ
7= የሚያስፈልገኝን መድኃኒት አገኛለሁ ብዬ ስለማልገምት
8= ሌላ

1= ከቤቶች አካባቢ ራቅ ባለ ቦታ
2= ከጓሮ/ከግቢ ውስጥ/
3= በሽንት ቤት (መፀዳጃ ጉድጓድ)
4= ሌላ

1= የጤና ባለሙያ
2= የቀበሌ ጤና ተጠሪ
3= ባሕላዊ አዋላጅ
4= የማዋለድ ሙያ የሌላቸው
5= ማንም አላዋለደኝም